ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 005 መስከረም 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የአሸባሪው ትሕነግ መሪዎች አእምሮ በጦርነት ያደገ በመሆኑ ሰላምን አይቀበልም

**ሙሳ ሙሐመድ**




አዲስ አበባ፡- የአሸባሪው ትሕነግ መሪዎች አእምሮ በጦረኝነት አስተሳሰብ በነውጥና በእምቢተኝነት ያደገ ቡድን በመሆኑ ምንም ያህል ስለሰላም ቢነገረው ከጦርነት ውጪ ሰላማዊ መንገድን ሊከተል እንደማይችል የስነልቦና ባለሙያው ተናገሩ። የአሸባሪው ትህነግ መሪዎችም ቀድሞም ለሰላምና ልማት የአዕምሮ ዝግጁነት ስለሌላቸው ወደሰላም ሊመለሱ አይችሉም ብለዋል።

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልቦና ትምህርት መምህሩና በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪው አቶ ወንድወሰን አያሌው እንደተናገሩት፣ የሕወሓት ቡድን ቀድሞውኑ እድገቱ ከሰው ተገልሎ በተንኮልና በሴራ ነው። አሁን ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ለሚፈልጉት ሰላምና ልማት መምጣት የአዕምሮ ዝግጁነት አልነበረውም፤ አሁንም የለውም።

ቡድኑ ከብጥብጥና ውዥምብር ጥቅሙን የሚያገኝ ነው ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ አባላቱም ሁሌም እራሳቸውን ብቻ አዋቂ አድርገው የሚያስቡ እና ለሌላ ሃሳብ ዝግ የሆነ አእምሮ ያላቸው ናቸው ብለዋል።

አቶ ወንድወሰን እንዳሉት፤ የቡድኑ አባላት ከጅምሩም የሰው ፍቅር አያውቁም፤ ገና ከልጅነታው ጀምሮ እስከ እርጅና ዘመናቸው በመግደልና በማሰቃየት የኖሩ ስለሆነ ለሰው ልጅ የሚያዝን ልቦና የላቸውም፤ በአንጻሩ አእምሮአቸው የሚረካው በጉልበታቸው የሚፈልጉትን ነገር ሲያደርጉ ነው ብለዋል።

የስነልቦና ምሁራን እንደሚሉት፤ የሰው ልጅ በልጅነቱ ጀምሮ በጫናው ውስጥ ከኖረ በሚያድግበት ወቅት እሱም ያንን ባህርይ ያንጸባርቃል፤ በዚህም የተነሳ ከፍ ሲልና ዕድሉን ሲያገኝ እሱ ራሱ አምባገነንና ነውጠኛ ይሆናል። የሕወሓት መሪዎችም ከልጅነታቸው ጀምሮ መሣሪያ አንግበው በነውጥ የኖሩ በመሆኑ አሁን ላሉበት ማንነት ምክንያት ሆኗቸዋል።

አቶ ወንድወሰን እንደሚሉት የቡድኑ አባላት

የአሸባሪው ትሕነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## “ዓስምአቀፉ ማህበረሰብ የጽንፈኛውን ትሕነግ ጠብ አጫሪነት ለይቶ ማውገዝ አለበት“

- አቶ ብናልፍ አንዷለም
የሰላም ሚኒስትር

ገጽ 4

# «የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ሊደርሱለት ይገባል»

- ለመከላከያ እጃቸውን የሰጡ የሸብር ቡድኑ አባላት

**ሙሉቀን ታደገ**

ወልቃይት፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ በአፋጣኝ ሊደርሱለት እንደሚገባ በወልቃይት ግንባር እጃቸውን ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የሰጡ የሽብር ቡድኑ ትህነግ አባላት ተናገሩ፡፡

ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እጃቸውን ከሰጡት መካከል የ54 ዓመቱ ጎልማሳ አቶ ገብረጊወርጊስ ገብረሥላሴ አንደኛው ናቸው፡፡ አቶ ገብረጊወርጊስ ገብረሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሽብር ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ቆርጦ ተነስቷል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የሽብር ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ ላይ የከፈተውን ዘመቻ በማስቆም ለትግራይ ሕዝብ በአፋጣኝ ሊደርሱለት ይገባል፡፡

የትግራይ ክልል በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የውጭ

ፎቶ ፡- እዮብ ተፈራ



ገብረጊወርጊስ ገብረሥላሴ



ኪሮስ በላይ



ጸጋ ትኩ

ወራሪዎች በተወረረ ሰዓት ሁሉም ኢትዮጵያውያን ከመላው የአገሪቱ ክፍል ከጫፍ ጫፍ ተነቃንቆ የትግራይን ሕዝብ እና መሬት ከወራሪዎች ነፃ አውጥቷል፡፡ አሁን ላይ የአገር ውስጥ ወራሪ የሆነው የሽብር ቡድኑ ትህነግ የትግራይ ክልልን በሕገወጥ መልኩ ወሮ ይዞ በትግራይ ሕዝብ ላይ በቃላት ሊገለጽ የማይችል በደል እየፈጸመ

«የኢትዮጵያ ሕዝብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሠራዊቱን መደገፍ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ጀግናውን የአገር መከላከያ ሠራዊት ደጀን ሆኖ መደገፍ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ነው ሲሉ የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ ተናገሩ፡፡ ለጀግናው የአገር መከላከያ

ሠራዊቱን መደገፍ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ኢትዮጵያ ከቡና ሀብቷ በሚገባ ለመጠቀም ዘርፋን በቴክኖሎጂ መደገፍ ይገባል

- ባለፈው አመት ከዘርፉ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል

ገጽ 3

# የፋብሪካዎች የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ይፋ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ከጊዜ ወደጊዜ እየናረ የመጣውን የሲሚንቶ ምርት ዋጋ ለማስተካከል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አዲስ ያወጣውን የፋብሪካዎች የሲሚንቶ የመሸጫ ዋጋ ይፋ አድርጓል።

ውሳኔው የተለያዩ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ ጥናት ላይ ተመስርቶ የተላለፈ መሆኑን እና በዚህ ጉዳይም ከፋብሪካዎች ጋር ውይይት መደረጉን የገለፁት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረመስቀል ጫላ፣ አሁን ላይ የሲሚንቶ ምርት እጥረት በመኖሩ ለመንግሥታዊ ሥራዎች ቅድሚያ እየተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ዋጋውን በራሳቸው እንዲወስኑ ዕድል ተሰጥቶ እንደነበርም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ገልጿል።

በዚህም መሠረት በኩንታል ደርባ ሲሚንቶ 590ነጥብ59፣ ዳንጎቴ ሲሚንቶ 549ነጥብ49፣ ኢትዮ ሲሚንቶ 595ነጥብ66፣ ሙገር ሲሚንቶ 643ነጥብ95፣ ሐበሻ ሲሚንቶ 683ነጥብ44፣ ናሽናል ሲሚንቶ 561ነጥብ39፣ ካፒታል ሲሚንቶ 633ነጥብ38፣ ኩዩ ሲሚንቶ 628ነጥብ10፣ ኢስት ሲሚንቶ 595ነጥብ66 እና ፒዮኒር ሲሚንቶ 510ነጥብ04 ብር እንዲሸጡ ተወስኗል።

ትላልቅ ፕሮጀክቶችም ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ማረጋገጫ በማምጣት ከፋብሪካዎች በቀጥታ ምርት የሚገዙበት መንገድ ተመቻችቷል ተብሏል።

በከተማ አስተዳደሮችና ክልሎች ይሁንታ ካገኙ አካላት ውጪ ሲሚንቶ ይዞ የሚገኝና በተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉ ግብይቶች ሕገወጥ በመሆናቸው ተቋሙ ማስታወቂያ ካስነገረበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ብለዋል።

የግል ተጠቃሚዎችን በተመለከተም የሁሉም ከተማ አስተዳደሮችና ክልሎች ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ስለሚታወቅ በመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በተደራጁ ማህበራት በኩል እንደሚያገኙ አስረድተዋል።

ኤፍቢሲ እንደዘገበው፤ በከተሞች ላይ የሚኖረው ሽያጭም የትራንስፖርት፣ የጫኝና አውራጅ እንዲሁም የመጋዘን ኪራይን ታሳቢ በማድረግ የሚሸጥ ይሆናል።

# በመሳው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉበት የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄ ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉበትና 500 ሚሊዮን ብር ለሰብዓዊ ድጋፍ ማሰባሰብን ታሳቢ ያደረገ የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄ ተጀመረ።

ንቅናቄው የተጀመረው ሦስተኛው ዙር ወረራን ተከትሎ በአገር ውስጥ ለሚከናወኑ ሰብዓዊ የድጋፍ ሥራዎች ሀብት ለማሰባሰብ የተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ባቀረበው ጥሪ መሠረት ከዳያስፖራው ድጋፍ ለማሰባሰብ ነው።

ንቅናቄው ይፋ በሆነበት ወቅት የገንዘብ ሚኒስትርና የብሔራዊ ሀብት አሰባሳቢ ኮሚቴ ሰብሳቢው አቶ አህመድ ሺዴ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ፣ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር መሀመድ እንድሪስ እንዲሁም በተለያዩ አገራት የሚገኙ የኢፌዴሪ አምባሳደሮችና ሚሲዮን መሪዎች ተገኝተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ በዚሁ ጊዜ ባስተላለፉት መልዕክት በአገር ውስጥ ሦስተኛው ዙር ወረራን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመከት እየተሠራ መሆኑን አንስተው፣ ሚሲዮኖችም በተለመደው ሁኔታ ዳያስፖራውን በማስተባበር ለሰብአዊ አገልግሎት አገር የምትፈልገውን ሀብት ለማሰባሰብ ትኩረት ሰጥተው ሊንቀሳቀሱ ይገባል ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በበኩላቸው በሚሲዮኖች አስተባባሪነት ዳያስፖራው ባከናወናቸው የሀብት ማሰባሰብ ተግባራት ባለፉት አራት አመታት ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆን ሀብት ማሰባሰብ መቻሉን አስታውሰው፣ የቀረበውን ወቅታዊ አገራዊ ጥሪ በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም ሚሲዮኖች ከዚህ በፊት ያካበቱትን ተሞክሮና ልዩ ልዩ የፈጠራ አግባቦችን በመጠቀም እንዲንቀሳቀሱ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር መሀመድ እንድሪስም ባለፈው በጀት አመት ለሰብዓዊ ድጋፍና ለአገራዊ ፕሮጀክት ከዳያስፖራው ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት መሰባሰቡን ጠቅሰው፣ የዳያስፖራውን አቅምና የሚሲዮኖችን የመፈጸም ችሎታ በሚገባ ማስተባበር ከተቻለ በብሔራዊ የሀብት አሰባሳቢ ኮሚቴ የተቀመጠውን ግብ ማሳካት እንደሚቻል ገልጸዋል።

የየአገራት አምባሳደሮችና የሚሲዮን መሪዎችም ገንዘቡን ከማሰባሰብ አንጻር ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ባሏቸው ጉዳዮች ላይ ጥያቄና አስተያየቶችን አቅርበው ከመድረክ ምላሽ ተሰጥቷል።

ሰሞኑን ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የተሳተፉባቸው የዘመን መለወጫና የአንድነት ቀን መርሀ ግብሮች በኢፌዴሪ ሚሲዮኖች አስተባባሪነት በተለያዩ አገራት በድምቀት መከበራቸውን ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ማህበራዊ ትስስር ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።



# የሸብር ቡድኑን በምርጫ ሥልጣን ከያዘ መንግሥት ጋር ማወዳደር ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው

*- ማቲው ኢህሬት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሽብር ቡድኑን በምርጫ ሥልጣን ከያዘ መንግሥት ጋር ማወዳደር ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ከመሆኑም ባለፈ መሬት ላይ ያለውን እውነት እና የአፍሪካ ኅብረትን ጥረት መካድ ነው ሲሉ በሞስኮ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ተመራማሪ ማቲው ኢህሬት ገለጹ። ኢትዮጵያ አሸባሪው ሕወሓት ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ የሚያሳስትበትን የመረጃ ጦርነት በተሟላ የመረጃ ትንተና ማክሸፍ እንዳለባትም አመልክተዋል።

ከፍተኛ ተመራማሪ ማቲው ኢህሬት እንደገለጹት፤ ከኢትዮጵያ ይልቅ አሸባሪው ሕወሓትን የመደገፍ አባዜ ኢትዮጵያን በብሔር ማንነት እና በተለያዩ ቡድኖች በማጋጨት ወደ ትንንሽ ግዛቶች ከፋፍሎ እንደፈለገ ለማስተዳደር ከሚመነጭ ፍላጎት ነው።

የሽብር ቡድኑን የተዛባ መረጃ በመቀበል ድጋፍ የሚያደርጉለት አንዳንድ ምዕራባውያን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አመራሮችን በተሟላ መረጃ መሞገት ይገባል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ክህደት ከፈፀመ በኋላ የሽብር ተግባሩን በማጠናከር በአማራ እና አፋር ክልሎች ወረራ በመፈጸም በንፁሃን ላይ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ጉዳት አድርሷል።

በንፁሃን ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመው ግፍ አልበቃ ብሎት ሐሰተኛ መረጃዎችን በማሠራጨት በመንግሥት የተጠቃ በማስመሰል ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ እያደናገረ ይገኛል።

መንግሥት የዘረጋለትን የሰላም እጅ በማጠፍ ሦስተኛ ዙር ወረራ የጀመረው የሽብር ቡድኑ ዛሬም እንደ ትናንቱ ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ለማሳሳት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ እየነዛ ነው።

በሞስኮ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ተመራማሪ ማቲው ኢህሬት እንደሚሉት፣ አሸባሪው ሕወሓት ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ የሚያደናግርበት መንገድ የመረጃ ጦርነትን በመጠቀም ነው።

በመረጃ ጦርነት ውስጥ ተገቢ ትንተና በማድረግ የሌሎችን የተሳሳተ መረጃ ማክሸፍ ካልተቻለ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የተዛባ ዕይታ መያዙ አይቀሬ ነው ይላሉ።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ብሎም አፍሪካውያን ያሉበትን ነባራዊ እውነታ ለዓለም ለማስተዋወቅ እና ተደማጭነታቸውን ለማሳደግ የመረጃ ጦርነትን ተንትኖ የማቅረብ ልምዳቸውን ማሳደግ ይገባቸዋል ብለዋል።

የሰላም ብያኔ በአገራት ብሔራዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ኢትዮጵያም በመረጃ ጦርነት የፈራረሰችው ሶሪያ ዕጣ እንዳይገጥማት የተደራጀ የመረጃ ትንትና ሥርዓት መዘርጋት እንዳለባት ጠቁመዋል።

ምዕራባውያን ከኢትዮጵያ ይልቅ አሸባሪው ሕወሓትን የሚደግፉት እንደ አገር አቅም ያለው መንግሥት እንዳይኖር እና ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ እና በቀጣናው ያላትን ተፅዕኖ ለማሳነስ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላት ተሰሚነት እንዳይጎላ እና የልማት ፕሮጀክቶችን በማሳካት ርሃብ እና ጦርነትን ለማጥፋት የጀመረችውን ጉዞ ለማደናቀፍ የታቀደ እኩይ ሴራ ነውም ብለዋል።

የሽብር ቡድኑ የጥፋት ዓላማውን ለማሳካት ሕፃናትን ለጦርነት እየመለመለ እና እየማገደ እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሠራተኞችን እያገተ በዝምታ የሚያልፉ ኃይሎች መኖራቸውን ጠቁመዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

ዜና

# ኢትዮጵያ ከቡና ሀብቷ በሚገባ ለመጠቀም ዘርፉን በቴክኖሎጂ መደገፍ ይገባል

## - ባለፈው አመት ከዘርፉ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን የቡና ሀብት በሚገባ ለመጠቀም ዘርፉ በቴክኖሎጂ ሊደገፍ እንደሚገባ ተገለጸ። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ 300 ሺ ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝታለች።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር «ቡናችን ለአብሮነታችንና ለብልጽግናችን» በሚል መሪ ቃል የቡና ቀን ከትናንት ጀምሮ እየተከበረ ነው።

በመክፈቻው ላይም ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ ከአንድ ሺ 500 በላይ የቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ዘርፍ የተሰማሩ አርሶ አደሮች፣ ቡና ላኪዎችና አቅራቢዎች የተገኙ ሲሆን፣ የፓናል ውይይትም ተካሂዷል።

በፓናሉ ላይ የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን ባደረጉት ንግግር፤ ቡና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንዳለው ጠቁመው፤ ቡና ኢትዮጵያ በውጭ ምንዛሬ ችግር ውስጥ በገባችበት ወቅት ለችግሯ ደራሽ ሆኗል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በቡናው ዘርፍ ያላትን አቅም በሚገባ ከመጠበቅ አንጻር ብዙ ክፍተቶች ስላሉ መሠራት አለበት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ያላትን የቡና ሀብት በሚገባ ለመጠቀም በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር፤ የዘንድሮው የቡና ቀን ለየት የሚያደርገው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሚከበር መሆኑ ነው ብለዋል። ለዚህም ከታች ከአርሶ አደሮች ጀምሮ እስከ ላኪዎች በትብብር በመሥራት እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በ2014 በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ 300 ሺ ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝታለች። ይሁን እንጂ ገቢው እንደ አገር ካለን ሀብት አኳያ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ያሳያል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከ6 ሺ በላይ የቡና ዝርያ ሲኖራት ለእያንዳንዱ የቡና ዝርያ ተስማሚ የአየር ንብረት አላት። ይሁን እንጂ ሀብቱን በሚገባ ከመጠቀም አንጻር ጉድለቶችን በማረም ሊሠራ ይገባል። ባለስልጣኑ አሠራሮችን በማዘመን ትኩረተ ሰጥቶ እየሠራ ነው። ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በሚገባ ለመጠቀም ዘርፉ በቴክኖሎጂ ሊደገፍ ይገባዋል።

ዶክተር አዱኛ እንዳሉት፣ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው 55 በመቶ የሚሆነው ቡና ጥራቱ የቀነሰ ነው። ይህን ለማሻሻል ልክ እንደ አየው የቡና እርሻ ልማት ቡናን በዘመናዊ መንገድ በማልማት፣ ገበሬዎች በክላስተር እንዲያለሙና ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የዓለም የቡና ዋጋ መዋዠቅ፣ የአየር ንብረት ለውጥና የደን ምንጠራ በኢትዮጵያ ቡና ላይ የተጋረጡ አደጋዎች ናቸው ያሉት ዶክተር አዱኛ፤ አደጋዎቹን ታሳቢ አድርጎ በመሥራት ዘርፉን በሚገባ ማልማት ላይ በሰፊው መሥራትን ይጠይቃል ብለዋል።

በ2013 በጀት አመት ወደውጭ የተላከው ቡና 248 ሺ 311 ነጥብ 66 ቶን ሲሆን ገቢውም 907 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ነበር፤ በ2014 ደግሞ 300 ሺ ቶን በመላክ አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

‹‹በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ›› ውድድር አንድ ኪሎ ቡና 47 ሺ 236 ነጥብ 23 ብር የተሸጠ እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር አዱኛ፤ የውድድሩ አሸናፊ አርሶ አደሮች እውቅና እንደሚሰጣቸውም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አህመድ በውይይቱ ወቅት እንደገለጹት፣ የቡና ሀብት በሚፈለገው ልክ ገቢ እንዲያስገኝ የሰላምና ጸጥታ ችግርና ተያያዥ ችግሮች ሊፈቱ ይገባል።



# የአፍሪካ ችግሮች በአፍሪካውያን እንደሚፈቱ ኢትዮጵያ የጸና እምነት አላት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ችግሮች በአፍሪካውያን እንደሚፈቱ ኢትዮጵያ የጸና እምነት እንዳላት በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ አስገነዘቡ።

አምባሳደሩ ቤጂንግ ለሚገኙ የአፍሪካ ሕብረት የሰላምና ጸጥታ ምክር ቤት አባላት እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተለዋጭ አባል በመሆን እያገለገሉ ለሚገኙ የአፍሪካ አገራት አምባሳደሮች በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ገለጻ አድርገዋል።

አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ባደረጉት ገለጻ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በአሸባሪው ሕወሓት አማካኝነት የተፈጠረውን ግጭት መንግሥት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ መሆኑን በአጽንኦት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካውያን ችግሮች በአፍሪካውያን እንደሚፈቱ የጸና እምነት እንዳላት አስገንዝበው፤ በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት ለሚደረገው የሰላም ድርድር ሂደት ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

አፍሪካውያን እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነትና በትብብር ከሠራን የሚያጋጥሙንን ችግሮች በቀላሉ መቅረፍ እንችላለን ብለዋል።

አምባሳደሮቹ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸው፣ ለዚህም ከኢትዮጵያ ጎን እንደሚቆሙ አረጋግጠዋል።

ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለው መርህ ወሳኝ ነው ማለታቸውንም በቤጂንግ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# በኮምቦልቻ የአሸባሪውን ትህነግ የጥፋት ተልዕኮ ለማስፈጸም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰርጎገቦች ተያዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኮምቦልቻ፡- የአሸባሪውን ትህነግ ተልዕኮ በማንገብ የተለያዩ የሽብር ተግባራትን ለመፈጸም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰርጎገቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ። የኮምቦልቻ ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ሰላም በማስጠበቅ ደጀንነታቸውን እያረጋገጡ መሆኑም ተገልጿል።

የከተማ አስተዳደሩ የጸጥታ ምክር ቤት ሰብሳቢና ከንቲባ አቶ መሐመድ አሚን ለኢዜአ እንደገለጹት፣ አሸባሪው ሕወሓት ለ3ኛ ጊዜ በከፈተው ጦርነት በግንባር የገጠመውን ሽንፈት ተላላኪዎቹ በሚፈጥሩት ውዥንብር ለማካካስ እየሠራ ነው።

የከተማውን ሰላም አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ እየተከናወነ ባለው ሕዝብን ያሳተፈ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በ15 ቀናት ውስጥ 105 ተጠርጣሪ ሰርጎ ገቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አቶ መሃመድ ገልጸው፤ ሰርጎ ገቦቹ የተለያየ መታወቂያ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የያዙ የባንክ ደብተሮች እንደተገኘባቸው ተናግረዋል።

ኅብረተሰቡ የሽብር ቡድኑን ሴራ ቀድሞ በመገንዘብ አካባቢውን ተደራጅቶ በመጠበቅ የከተማውን ሰላም የማረጋገጡን ሥራ አጠናክሮ እንዲቀጥልም አሳስበዋል።

ወጣቶች ተደራጅተው ከተማዋን ከመጠበቅ ባለፈ ለሠራዊቱ ትጥቅና ስንቅ እያደረሱ በመሆኑ ሊመሰገኑ ይገባዋል ብለዋል።

ከንቲባው አክለውም ኅብረተሰቡ የደጀንነት ሚናውን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን ገልጸው፤ በአውደ ግንባር የመከላከል ውጊያ ከጠላት ጋር እየተፋለመ ላለው ሠራዊት እያደረገ ያለውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።



**አቶ መሐመድ አሚን**

ከኮምቦልቻ ከተማ ነዋሪዎች መካከል ወይዘሮ አባይነሽ ፍስሃ በሰጡት አስተያየት፣ ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ሰላም ተደራጅተው በመጠበቅ ሰርጎ ገቦችን ለሕግ አሳልፈው እየሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብ በማስተባበር፣ ለአገር መከላከያ ሠራዊት ስንቅ በማዘጋጀትና የሽብር ቡድኑን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመመከት የደጀንነት ሚናቸውን እየተወጡ መሆኑንም አስረድተዋል።

«ሌት ተቀን አካባቢያችንን ነቅተን በመጠበቃችን የሽብር ቡድኑን ተልዕኮ ተቀብለው ለጥፋት ይሯሯጡ የነበሩ ሰርጎ ገቦች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ማድረግ ችለናል» ያለው ደግሞ ወጣት አረቡ አህመድ ነው።

ለጀግናው የአገር መከላከያ ሠራዊትና ሌሎች የፀጥታ አባላት የኋላ ደጀንነታቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ ግንባር ድረስ በመሄድ የሽብር ቡድኑን እኩይ ዓላማ ለማክሸፍ ዝግጁነቱንም አረጋግጧል።

ዜና



ፎቶ ፡- ገባው ገብሬ

# ሠራዊቱን መደገፍ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሠራዊት ከ118 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትና በሥሩ ያሉ 18 ያህል ተጠሪ ተቋማት፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የዳውሮና ኮንታ ዞኖች እንዲሁም የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ለጀግናው የአገር መከላከያ ሠራዊት ከ118 ሚሊዮን በላይ የዓይነትና ገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል፡፡

የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ ድጋፉን ከተቀበሉ በኋላ ሁሉም አካላት ለሠራዊቱ ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ወይዘሮ ማርታ እንደተናገሩት፤ ሠራዊቱ ለአገሪቱ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በመቆም ትልቅ ተጋድሎ እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ሕዝቡም ሠራዊቱን በመደገፍ ስንቅ በማቀበል የጎደለውንና የሚያስፈልገውን ሁሉ በማሟላት እየሠራ ነው፡፡ ሠራዊቱን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መደገፍ የኢትዮጵያን አንድነት፣ ሉዓላዊነትና ሠላም ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሠራዊቱ የአገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር ተጋድሎን እንደሚፈጽመው ሁሉ የቀረው ሕዝብም ሚናውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል፡፡ ሁሉም አካል ለሠራዊቱ ላደረገው ድጋፍ ምስጋና በማቅረብ፤ ድጋፉ ሠራዊቱ በግንባር ሆኖ ከጠላት ጋር በመዋደቅ ጀግንነትን በማስመስከር ድል እንዲያገኝ እያገዘ እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

«በቀጣይም በተሰጠን ተልዕኮ፣ ባለን የመንግሥት የሥራ ኃላፊነት፣ እንዲሁም አጠቃላይ ማህበራዊ አገልግሎት ከጎናችን ያሉትን ሠራዊቱንና ቤተሰቦቻቸውን በመደገፍ፤ ከእኛ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸውንና ልናግዛቸው የሚገባቸውን ሁሉ በማገዝ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የግዛት አንድነትና ሠላም አብረን እንድንቆም፤ በቀጣይም በዚህ መንፈስ ተጠናክረን እንድንቀጥል አደራ እላለሁ» ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ጳውሎስ በበኩላቸው፤ የአገርን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ መላው የአገሪቱ ሕዝቦች የራሳቸውን ሚና እየተወጡ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትም በሥሩ ካሉ ተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን በሁሉም አውዶች ድጋፉን በማድረግ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል፡፡

በትናንትናው ዕለት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትና በሥሩ የሚገኙ 18 ተጠሪ ተቋማት 90 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር እንዲሁም የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ሁለት ሚሊዮን ብር ለጀግናው የአገር መከላከያ ሠራዊት የሰጡ ሲሆን፤ ይህም ደረቅ ምግቦች፣ ሰንጋዎች፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና አልባሳትን ያካተተ ድጋፍ ነው፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከዳውሮና ኮንታ ዞን ሕዝብ ያሰባሰበውን 361 ሰንጋዎች፣ 33 በግ እና ፍየል በአጠቃላይ ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ አድርጓል፡፡

# የአሸባሪው ትሕነግ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አዕምሯቸው ያደገው በጥፋትና በማፍረስ ነው። አሁን ያሉበት ሁኔታ ይህንኑ የሚያንጸባርቅ ነው።

በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነት ሰዎች ለህሊናቸው ታማኝ አይደሉም። የሕወሓት መሪዎችም የዚህ ባህርይ ተጠቂዎች ናቸው። ለምሳሌ የአገር ሰላምን ፈላጊ ለመምሰል የማይተገበሩ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ በሚቃረኑ ቃላቶች የሕዝቡን ሥነ-ልቦናና ስሜት ለማግኘት ይጥራሉ፤ ለነሱ ፍላጎት እስከጠቀመ ድረስ ለመዋሸትም ሆነ እርስ በርስ የሚጣረሱ ሃሳቦችን ለማውራት ፈጽሞ ይሉኝታና ዴንታ የላቸውም።

ቡድኑ የአገር ሰላምና ልማትን የማይሻ ነው። አገርንና ዜጋን ጠል አዕምሮና ስነ-ልቦና ያላቸው ሰዎች ስብስብ ስለሆነ ተግባራቸውም የዚሁ ውጤት ነው ብለዋል።

ቡድኑ በኢትዮጵያ ላይ ለሚሠራው ሴራ የሚመቸውን የስነ-ልቦና ስሜት ለውጥ ለማምጣት በየጊዜው እርስበርሳቸው የሚጣረሱ ቃላቶችን በመናዘዝ የዓለምን ሕዝብና ነዋሪዎችን ያወዛግባል። ይህ ደግሞ ከባህርይው የሚመነጭ ስለሆነ አዲስ አይደለም። ለዓመታት የዓለምን ሕዝብም ሳይቀር ሲያሳስት ኖሮበታል ብለዋል።

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፣ በሚቃረኑ ቃላቶቹ ሊሰበር የሚችል ስነ-ልቦናና ስሜት በኢትዮጵያ ሕዝቡ ዘንድ የለም። ማኅበረሰቡ የቡድኑን ሰላም ጠልነት ጠንቅቆ አውቆታል።

የቡድኑ የሚያወናብዱ ቃላት ከቡድኑ መሪዎች የስነ-ልቦና ቀውስ የሚመነጭ ነው። በዚህም የአገሪቱን ልማትና እድገት ለማደናቀፍ በየዕለቱ የሚቃረኑ ቃላቶች መለያና ኑዛዜዎቹ አድርጓቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በማኅበረሰቡ ዘንድ እነሱ የሰላምንና የልማት ፍላጎት ያላቸው ለመመስል ነው የሚጥሩት። አሁን ላይ የዜጋና አገር ጥላቻ ያነገቡ መሆናቸው የሕዝቡ አዕምሮ ተረድቷልም ብለዋል።

በተራዘመው ጦርነት በሰዎች ላይ የፈጸሟቸው ዘግናኝ ድርጊቶችን ላዩ፣ ለሰማና ለሚያውቅ ሕዝብና ማኅበረሰብ ምንም ቢሉ ስነ-ልቦናውና ስሜቱን ሊከፍትላቸው እንደማይችል ስለሚያወቁ ጦርነትን የሙጥኝ በማለት ከጦርነት ወደ ጦርነት ይገባሉ። ይህንም የስልጣን ቆይታቸውን ማራዘሚያ አድርገውታል ብለዋል።

ለድርድር ሲጠራ ጦር ያነሳ ቡድን በየትኛውም ሰውና ማኅበረሰብ ዘንድ በየትኛውም የቃላት ሽንገላ ስነ-ልቦናውና ስሜቱ ሊከፈት አይችልም ሲሉ አቶ ወንድወሰን ገልጸዋል።

ማኅበረሰቡ የሚሉትንና የሚተገብሩትን ሁለቱን ለይቶ መሬት ላይ ያለውን ሀቅ ማወቅ አለበት ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ የሚናገሩትንና በምድር ላይ የሚተገበሩትንም ፈጽሞ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ማገናዘብ ይገባል ብለዋል።

የተጠቂው ማኅበረሰብ፣ የክልሎች ሕዝብና የፌዴራል መንግሥት ሀቁን ከለዩ የሚቃጡትንና የሚመጡበትን መንገድ በራሱ ለመቀልበስ በቂ ስንቅ ይሆናል ሲሉ አቶ ወንድወሰን አመላክተዋል።

# «ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የጽንፈኛውን ትሕነግ ጠብ አጫሪነት ለይቶ ማውገዝ አለበት»

**- አቶ ብናልፍ አንዷለም**
**የሰላም ሚኒስትር**

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ያለውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት የዓለም ማኅበረሰብ ተገቢውን እውቅና እና ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና፣ የፌዴራል መንግሥትንና የአሸባሪውን ቡድን እኩል ተጠያቂ ማድረግ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የጽንፈኛውን ቡድን ጠብ አጫሪነት ለይቶ ማውገዝ አለበት ሲሉ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም ተናገሩ፡፡

የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን መረጋጋት ለአፍሪካ ቀንድ የሰላም መሠረት አድርጎ በመቁጠር ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚያደርገውን ገንቢ ድጋፍ በአገሪቱ ዘላቂ መረጋጋትን በሚያመጣ መልኩ ማድረግ አለበትም ብለዋል።

ሚኒስትሩ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፣ ወቅቱ በዓለማችንም ሆነ በአካባቢያችን የሚታዩ የጸጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሰላም ኃይሎች ጋር በትብብር መሥራት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። በመሆኑም የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት አለበት።

እንደ አቶ ብናልፍ ገለጻ፣ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ከፈለገ የግጭቱ አነሳሽ የሆነውን አሸባሪውን ሕወሓት በመለየትና ከማውገዝ ተጨማሪ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ጫና ማድረግ አለበት። አንዳንድ የዓለም ኃያላን አገራትም መንግሥት በተደጋጋሚ ያቀረባቸውን የሰላም ጥሪዎች በመረዳት ተገቢውን እውቅና መስጠት አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያን ሰላም ማረጋገጥ የሚቻለው የግጭቱ ዋና ፈጣሪ ሲወገዝ እና ወደ እውነተኛ ሰላም እንዲገባ ሲደረግ ነው ያሉት አቶ ብናልፍ፣ ለቀጣናው መረጋጋት የኢትዮጵያ ሰላም መስፈን አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና 120 ሚሊዮን እና ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያላት አገር ናት። አገሪቷ ሰላም እንድትሆን ከተደረገ ቀጣናው ሰላም የሚሆንበት ዕድሉ ሰፊ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ብናልፍ ገለጻ፣ በእያንዳንዱ የሰላም እጦት ሊጎዱና ከፍተኛ መስዋት ሊከፍሉ የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ናቸው። ነገር ግን የችግሩ ተጠቂ ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም። የአፍሪካ ቀንድ አገራትም የችግሩ ተጋላጭ የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የራሷን ሰላም ከመጠበቅ ባሻገር በዓለም የሰላም ማስከበር ሥራዎች ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች ያሉት አቶ ብናልፍ፣ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በሚመለከት አንዳንድ የውጭ ኃይሎች አካሄድ ለአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መልካም አይደለም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ሰላምንና መረጋጋትን ከማስጠበቅ በተጨማሪ በዓለም የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች የመሳተፍ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላት አገር ናት ያሉት አቶ ብናልፍ፣ በተለያዩ የአፍሪካ አገራት የተፈጠሩት ችግሮች እንዳይባባሱ በማድረግ የበኩሏን ስታደርግ የቆየች አገር ናት ብለዋል።

በዓለም ላይ ለስደት የተዳረጉ አገሮችን ብንመለከት ለስደታቸው መንስኤ ጦርነት ነው ያሉት አቶ ብናልፍ፣ ጦርነት የጉዳቶች ምንጭ እንጂ የመፍትሄ መሠረት አይደለም። ኢትዮጵያ ለሰላም ምንጊዜም በሯ ክፍት ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን መንግሥት ጥረት ቢያግዝ ለቀጣናው ዘላቂ ሰላም ይገኛል ሲሉም አጽንኦት ሰጥተዋል።

# «የኢትዮጵያ ሕዝብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ይገኛል።

ስለሆነም አሁንም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከዚህ ቀደም እንደሚያደርገው ከጫፍ ጫፍ ተነቃንቆ የትግራይን ሕዝብ ከሰቆቃ ኑሮ እንዲያላቅቀው ጥሪያቸውን አቅርበዋል። የትግራይ ወጣቶችም የሽብር ቡድኑን ለመደምሰስ ለሚደረግ ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ መከላከያ ጎን በመሰለፍ የትግራይ ሕዝብን የስቃይ ጊዜ ማሳጠር እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

እንደ አቶ ገብረጊወርጊስ ገለጻ፤ የሽብር ቡድኑ ሁሉንም የትግራይ ክልል ነዋሪዎች ከሕፃናት እስከ አዋቂ ብሎም ከወጣት እስከ አቅመ ደካሞች ወደ ጦር ግንባር እያዘመተ ይገኛል። በዚህም በርካታ የትግራይ እናቶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ እና አረጋውያን አላማ ለሌለው ሞት እንዲሞቱ ተፈርዶባቸዋል።

የሽብር ቡድኑ መጀመሪያ ላይ ሁለት ልጆቻቸውን ለእኩይ ተግባሩ ነጥቆ እንደወሰደባቸው የሚናገሩት አቶ ገብረጊወርጊስ፤ አሁን ደግሞ ራሳቸውን የቤቱ አባወራ ካልዘመቱ ለቤተሰብ እርዳታ አልሰጥም በመባላቸው ሕፃናት ልጆቻቸውን እና ባለቤታቸውን ከርሃብ ለማትረፍ ሲሉ ተገደው የሽብር ቡድኑን መቀላቀላቸውን ጠቁመዋል።

የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎችን እንዳይማረኩ ለማድረግ በመከላከያ የተማረኩ ሰዎች በርካታ ሰቆቃዎች እንደተፈጸመባቸው አድርጎ ይሰብካል ያሉት አቶ ገብረጊወርጊስ፤ ይህ የሽብር ቡድኑ ስብከት ፈጽሞ ሃሰት መሆኑን በመረዳት ሁሉም የትግራይ ወጣት በአፋጣኝ ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እጃቸውን እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

ሌላውኛዋ ለመከላከያ እጇን በመስጠት ሕይወቷን ማትረፍ የቻለችው በአክሱም ከተማ ተወልዳ ያደገችው የ16 ዓመት ታዳጊዋ ጺጋ ትኩ በበኩሏ፤ የሽብር ቡድኑ ባወጣው «አንድ ታጣቂ ከአንድ ቤት» ሕገወጥ መመሪያ ዕድሜዋ ለጦርነት ሳይደርስ የመጀመሪያ ልጅ ስለሆነች ብቻ ቤተሰቦቿ ተገደው የሽብር ቡድኑን እንድትቀላቀል መደረጓን ትናገራለች።

የሽብር ቡድኑ በትግራይ ክልል ነዋሪዎች ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ የትግራይን ሕዝብ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የሚመስል ነው ያለችው ጺጋ፤ ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሽብር ቡድኑን ድርጊት በአፋጣኝ በመቀልበስ የትግራይን ሕዝብ ከሽብር ቡድኑ ግድያ እና ጭቆና ሊታደገው እንደሚገባ አመላክታለች ።

የሽብር ቡድኑ የፖለቲካ ሰዎች ስብከት እጅግ አደገኛ ነው የምትለው ጺጋ ፤ የመከላከያ ሰራዊት ከማረካችሁ ተቆራርጣችሁ ትጣላላችሁ እየተባሉ እንደሚነገራቸው እና አብዛኛው የትግራይ ወጣትም ጦርነቱን ቢጠላም ለመከላከያ እጁን መስጠትን ግን አጥብቆ እንደሚፈራ ተናግራለች።

አሁን ላይ በመከላከያ ሰራዊት እየተደረገላት ለሚገኘው ድጋፍ እጅጉን ያመሰገነችው ጺጋ፣ የትግራይ ወጣቶች የሽብር ቡድኑ የሚነግራቸው ፕሮፓጋንዳ ፍጹም ውሸት መሆኑን ተረድተው አሁኑኑ ለመከላከያ እጃቸውን በመስጠት ሕይወታቸውን እንዲያተርፉ ጥሪዋን አቅርባለች።

ሌላኛው ለመከላከያ እጃቸውን የሰጡት የ75 ዓመት አዛውንቱ አቶ ኪሮስ በላይ በበኩላቸው፤ የሽብር ቡድኑ ትህነግ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው በደል ከትግራይ ሕዝብ ማህጸን በወጡ ኃይሎች ነው ብሎ ለማመን እንደሚቸገሩ ይናገራሉ።

ከጦርነቱ በፊት አምስት ልጆች ነበሩኝ ያሉት አቶ ኪሮስ፤ በሽብር ቡድኑ ተገደው ሁሉንም ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ጦርነት እንዲገቡ መደረጋቸውን ይናገራሉ። አቶ ኪሮስ ተገደው ወደጦርነት ሲገቡ በዕድሜ መግፋት እና በህመም ብዛት እንደልባቸው መንቀሳቀስ የማይችሉት ባለቤታቸው ቤት ብቻቸውን እንደቀሩ ይናገራሉ። አሁን ላይ ባለቤታቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ እንደማያውቁ እና በዚህም የመረረ ኀዘን ውስጥ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

በትግራይ ክልል የሰው ልጅ ከሰውነት ክብሩ እጅጉን ወርዶ ይገኛል ያሉት አቶ ኪሮስ፤ የሽብር ቡድኑ ትህነግ በትግራይ ሕዝብ ላይ ከዚህ የበለጠ እልቂት ከመፈጸሙ በፊት ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት በፍጥነት ለትግራይ ሕዝብ ሊደርስለት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፀጥታው ምክር ቤት በአገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ ይከበር!

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ለዓለም ሰላምና መረጋጋት ስጋት የሆኑ ችግሮች ላይ በመምከር መፍትሄ የማፈላለግ ኃላፊነት የተጣለበት ዓለም አቀፍ ተቋም ነው። ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት የሚያስችሉ አሠራሮች፣ ደንቦችና የመተዳደሪያ ቻርተርም አለው። የሥራው ውጤታማነት የሚመዘነው ለሚገዛበት አሠራሮች፣ ደንቦችና ለሚተዳደርበት ቻርተር ታማኝ ሆኖ በተገኘበት ልክ ነው።

ኢትዮጵያ እንደ አገር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መስራች አባል አገር እንደመሆኗ መጠን፤ ተቋሙ ለዓለም ሰላም የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በመቀበል ለተግባራዊነቱም ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ስትንቀሳቀስ ቆይታለች። ይህ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሆና በሠራችባቸው ወቅቶች ጭምር በተግባር የታየ ነው።

አገሪቱ ለምክር ቤቱ አሠራሮች፣ ደንቦችና ለሚተዳደርበት ቻርተር ተገዥ በሆነችበት ለዓለም ሰላም ያላት ቁርጠኝነት ባልተለወጠበት፣ ስለ ሰላም ሲባል በብዙ የሰላም ማስከበር ዘመቻዎች ተሰማርታ መስዋዕትነት እየከፈለች ባለችበት ሁኔታ፣ የጸጥታው ምክር ቤቱ ባልተለመደ እና ባልተገባ መልኩ የአገሪቱን የውስጥ ጉዳይ አጀንዳ አድርጎ ማየት ከጀመረ ዓመታት እየተቆጠሩ ነው።

ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ እንደሚረዳው በኢትዮጵያ እየሆነ ያለው አንድ አምባገነናዊ ሥርዓት በሕዝብ እንቢተኝነትና ትግል ከሥልጣን ተወግዶ አዲስ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በቦታው የመትከልና የማጽናት ሥራ ነው። ይህ በየትኛውም የዓለም ክፍል በተለያዩ ወቅቶች የተከናወነ፤ የአገራት የውስጥ ጉዳይ ተደርገው የሚወሰድ ነው። እንኳን አሁን ባለንበት ስለ ዴሞክራሲና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ብዙ ድምፆች በሚጮሁበት ዘመን ቀርቶ፣ በቀደሙት ዘመናት ሕዝቦች ከውስጣቸው በመነጨ የለውጥ መሻት ያካሄዷቸው የለውጥ ትግሎች የምክር ቤቱ አጀንዳ ሆነው አያውቁም፤ ወደ ፊትም ከድርጅቱ የመተዳደሪያ ቻርተር አንጻር አጀንዳ ሊሆኑ የሚችሉበት ተጨባጭ ምክንያት አይኖርም።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እንደሚስተዋለው ግን አንዳንድ አገራት የኢትዮጵያን ጉዳይ ዓለም አቀፍ የጸጥታና ደኅንነት ስጋት ይሆናል በሚል ጉዳዩን ከራሳቸው ፍላጎት አንጻር በማየት የሽብርተኛው የትህነግ ቡድንን ጉዳይ ይዘው ወደ ጸጥታው ምክር ቤት መሄድ ሥራቸው አድርገውታል።

ላለፉት ሁለት ዓመታት የዓባይ ግድብ ጉዳይን ሳይጨምር በኢትዮጵያ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ብቻ ምክር ቤቱ ለ12ኛ ጊዜ ስብሰባ ጠርቷል። በጉዳዩ ዙሪያ ያልተገቡ የውሳኔ ሀሳቦችን ለማስተላለፍ የተደረጉ ሙከራዎችም ነበሩ።

የምክር ቤቱ አጀንዳ እየሆነ ያለው አሸባሪው ትህነግ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በመንግሥትና በሕዝብ የተሰጠውን የሰላም አማራጮች ወደ ኋላ በመተው፤ ያጣውን ስልጣን በኃይል ለማስመለስ በጦርነት ውስጥ አገርና ሕዝብን ከቶ አላስፈላጊ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኝ ጸረ-ሰላም ኃይል ነው። የዚህን እኩይ ቡድን ዓላማ መዋጋት እና ማምከን የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ ጉዳይ እና ምርጫ ብቻ ነው።

ይህ ጉዳይ ለውጡን ብዙ መስዋእትነት ከፍሎ ያመጣው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጉዳይ ነው። ስለሆነም በየትኛውም መመዘኛ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ሊሆን አይችልም። በተለይም የጸጥታው ምክር ቤት አጀንዳ የሚሆንበት የአሠራር፣ የሕግም ሆነ የሞራል መሠረት የለውም። አጀንዳ መሆን የሚገባው ሕፃናትን፣ ታዳጊዎችን፤ አረጋውያንና መነኮሳትን ሳይቀር በኃይል አስገድዶ ለጦርነት እያሰለፈና እየደፈረ ያለው የሽብር ቡድኑ ነው።

ቡድኑ በንጹሃን ላይ ከባድ መሣሪያዎችን በመተኮስ የሚያደርሳቸው አሰቃቂ የጭካኔ ተግባራት፣ ውድመትና መፈናቀሎች እጅግ ብዙ ናቸው። መንግሥት እንደመንግሥት የተጣለበትን የአገር ሉአላዊነት ማስከበርና የሕዝቦችን ሰላም የመጠበቅ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያደርጋቸው ጥረቶች የምክር ቤቱ አጀንዳ ሊሆኑ አይገባም።

የቡድኑ ዓለም አቀፍ የፕሮፓጋንዳ ማሽነሪዎች ቡድኑ ሽንፈት ሲገጥመው የቅጥፈት ወሬ እየፈበረኩ በተቀጣሪ የመገናኛ ብዙኃን ሠራተኞችና ሎቢስቶች የሚያካሂዷቸውን ዘመቻዎች ዱካ እየተከተሉ አገሪቱን የምክር ቤቱ አጀንዳ የማድረጉ ጉዳይ ከምክር ቤቱ ተልዕኮና መርህ የሳተና በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ከመሆኑም በላይ ምክር ቤቱ የቱን ያህል ባልተገቡ ተግባሮች ራሱን እያስገባ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

ሰሞኑን በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል አሸባሪው ትህነግ እየፈጸመ ያለውን ሦስተኛ ዙር ወረራ መንግሥት እየተከላከለ ባለበት ሁኔታ የሽብር ቡድኑን ማውገዝ ሲገባ ችግሩን ዓለም አቀፍ የጸጥታና ደኅንነት ስጋት የሆነ እስኪመስል ድረስ የምክር ቤቱ አጀንዳ አድርጎ ስብሰባ ለመጥራት የሄደበት መንገድ በተመሳሳይ መልኩ ሕጋዊ መሠረት የሌለውና ከምክር ቤቱ መርህ ያፈነገጠ ነው። አሁን በአገሪቱ ያለው ችግር የውስጥ ጉዳይ እንደመሆኑ አገሪቱ ችግሮቿን በራሷ የመፍታት ሉዓላዊ መብት አላት፤ እያደረገች ያለውም ይህንኑ ነው::

ችግር አለ ተብሎ ከታሰበም ጉዳዩ መታየት ያለበት በአፍሪካ ኅብረት በኩል ነው ፤ በአፍሪካ ኅብረት የሰላምና ጸጥታ ምክር ቤትና በመንግሥታቱ ድርጅት በኩል ያለው ግንኙነት የሚወሰነውም በዚሁ መርህ ነው። ስለሆነም የጸጥታው ምክር ቤት ከምርሁ ካፈነገጠው ይህን መሰል ዝንፈት ሊታቀብ ይገባል።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የአሸባሪው ትህነግ የጭካኔ ጥጎች

አሲ ሴሮ

ብዙዎች ከናዚ ጀርመን ጋር ያመሳስሉታል። አንዳንዶቹ ከካንቦዲያው አማጺ ኬምሩዥ ጋር ይወግኑታል። ከቦኮሃራምና ከአልሻባብ ጋርም የሚያነጻጽሩት አሉ። ያም ሆነ ይህ ግን አሸባሪው ትህነግ የለየለት አረመኔ መሆኑን ሁሉም በአንድ ድምጽ ይስማማሉ። ለዚህ አንዱ ማሳያ ደግሞ ከቅርቡ እንጀምር ብንል እንኳን ሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሪፖርተሮች በአካል በመገኘት ያረጋገጡት የሽብር ቡድኑ የጭካኔ ተግባር አንዱ ነው።

እማሆይ ማይጠምቱ ገብረ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እጃቸውን ከሰጡ አንዱ ናቸው። ጨካኙ አሸባሪው ትህነግ የ75 አመት አዛውንቷን ለጦርነት መልምሎ አሰልፏል። መነኩሴዋ ለጦርነት ሲመለመሉና ለግዳጅ ሲላኩም እንደማንኛውም መነኩሴ የጸሎት ማድረሻ መቁጠሪያ አድርገዋል፤ የምንኩስና ቆብም ደፍተዋል።

እማሆይ ማይጠምቱ በእዚህ ዕድሜያቸው ቤተክርስቲያን ሄደው ለራሳቸውም፤ ለአገራቸውም ጸሎት ከማድረግ ይልቅ በጦር ሜዳ ተገኝተው ቦምብ እንዲወረውሩ በቡድኑ ተፈርዶባቸዋል። ተነግሮ የማያልቀው አሸባሪው ትህነግ የጭካኔ ተግባራት በእማሆይ ማይጠምቱ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። አይነስውራንን ጭምር በጦር ሜዳ በማሰለፍ ነውረኛ መሆኑን በተጨባጭ አሳይቷል። ለዚህ ሌላው አብነት የሚሆኑት በሕፃናት እየተመሩ ቦምብ ታጥቀው በጦር ሜዳ የተገኙትና እጃቸውን ለመከላከያ ሰራዊት የሰጡት የ72 አመቱ አይነስውር አረጋዊ አቶ ተክለኃይማኖት ተስፋዬ ናቸው።

የሽብር ቡድኑ የጭካኔ ተግባራት ዘመን ተሻጋሪና ከቡድኑ አፈጣጠር ጀምሮ የነበረ ነው። በወቅቱ የነበረውን መንግሥት ለመቃወም ወደ ትግል ሜዳ ከወጡት መሃል የትግራይ ነፃነት ግንባር የሚባል ድርጅት አንዱ ነበር። ማንም ተቀናቃኝ ከጎናቸው እንዲኖር የማይፈልጉት የቡድኑ አባላት እንመካከር በሚል ሽፋን የትግራይ ነፃነት ግንባር አባላትን በአንድ ቦታ በመሰብሰብ በተኙበት ለወሬ ነጋሪ ሳይቀሩ ሁሉንም ጨርሰዋቸው አድረዋል። በ17 አመታቱ ጦርነትም የቡድኑን አካሄድ የተቃወሙ በርካታ የትግራይ ንጹሃን ልጆች በጠራራ ፀሐይና በጠፍ ጨረቃ በሽብር ቡድኑ ተረሽነዋል።

አንዳንዶችንም ቡድኑ ለማሰቃያ አላማ ባዘጋጀውና ባዶ ስድስት በሚባለው እስር ቤት ለአመታት እንዲማቅቁ በማድረግ ለአካልና ለሥነልቦና ጉዳት ዳርገዋቸዋል። በየበረሃው ባቋቋማቸው ከምድር በታች እስርቤቶችም በርካቶችን በመግረፍና በማሰቃየት የጭካኔ ጥሙን ሲወጣ ቆይቷል።

የአሸባሪ ቡድኑ አባላት ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላም ስልጣናቸውን የሚገዳደሩ ሰዎችን እራሳቸው ባቋቋሟቸው ድብቅ እስር ቤቶች በማሰቃየት የማፍያ ሥራ ሲሠሩ ኖረዋል። በማዕከላዊ እስር ቤትም በርካታ ንጹሃን ዜጎችን በማጎርና በማሰቃየት ትውልድ ይቅር የማይለው ግፍ ፈጽመዋል።

በወንዶች ብልት ላይ የሃይላንድ ውሃ በማንጠልጠልና በማኮላሸት፤ በሴቶች ላይም ከኢትዮጵያዊ ሥነምግባር ውጪ የሆኑ ጸያፍ ተግባራትን ሲፈጽሙ ኖረዋል። ስልጣናችንን ይገዳደረናል የሚሉትን ግለሰብ ሳይቀር ሽብርተኛ የሚል ተቀጽላ በመለጠፍ የፊጥኝ አስረው አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ሲያደርሱ ኖረዋል። አማራውን ግንቦት ሰባት፤ ኦሮሞውን ኦነግ በሚል ዜጎች በአገራቸው ላይ በነፃነት ሃሳባቸውን እንዳይገልጹና በብሔራቸው ተሸማቀው እንዲኖሩ አበክረው ሰርተዋል።

በስልጣን ማብቂያቸው ዘመን አካባቢ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተነሳውን የሕዝብ ተቃውሞ በኃይል ለማፈን ሲባል በርካታ ወጣቶች እንደቅጠል እንዲረግፉ ተደርጓል። በወለጋ አካባቢ አንዲት እናት ልጇን ገድለው በሬሳው ላይ እንድትቀመጥ ያደረጉበት አጋጣሚ እስካሁንም ከሕዝብ ህሊና የሚፋቅ አይደለም።

የስልጣን ዘመናቸው አብቅቶ መቀሌ ከመሸጉ በኋላም ለ20 አመታት ያህል ሲጠብቃቸው የቆየውን የሰሜን ዕዝን ከጀርባው በመውጋት ወራዳ ተግባር ፈጽመዋል። ቀን የአርሶ አደሩን ሰብል ከአንበጣ ሲከላከሉ የዋሉትን የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሌሊት በተኙበት በማረድ የሽብር ቡድን አረመኔነቱን አሳይቷል። ሴት የመከላከያ ሰራዊት አባላትን ጡት በመቁረጥ የጭካኔያቸውን ጥግ ገልጸዋል። የሞቱ የሰራዊቱን አባላት ልብስ አውልቀው በፀሐይ በማንቃቃት በሬሳ ፊት ከበሮ ደልቀዋል።

በትግራይ ብልጽግና ፓርቲን ትደግፋላችሁ በሚል ብዙዎችን በገፍ ገድለዋል። ከዚያም አልፎ ሬሳቸውን ከጉድጓድ በማውጣት ለጅብ አስበልተዋል። እርጉዝ ሴቶችን በሳንጃ በመውጋት አረመኔነታቸውን በአደባባይ አሳይተዋል። የመከላከያ ሰራዊት ከመቀሌ ከወጣ በኋላም በአማራና በአፋር ክልል ወረራ በማድረግም በሕዝቦች ላይ መጠነ ሰፊ ግፍ ፈጽመዋል። ሕፃናትና የ80 አመት መነኩሴን ጭምር በመድፈር ነውረኛነታቸውን አሳይተዋል። ከሰዎች አልፈው እንስሳትን ጭምር በጥይት ደብድበው በመግደል የጥላቻቸውን ጥግ አስመስክረዋል።

በተለይም በማይካድራ ብሔርን መሠረት ባደረገ መልኩ ሳምሪ የሚባል የወጣቶች ጨፍጫፊ ቡድን በማቋቋም ከ1ሺ 500 በላይ አማሮች በጅምላ ፈጅተዋል። በጭና ሰፊ ጭፍጨፋ አድርገዋል። በአፋር ጋሊኮማ ሕፃናትንና ሴቶችን በከባድ መሣሪያ ገድለዋል። በአማራና በአፋር የሃይማኖት ተቋማት ላይ ጭምር በመጸዳዳትና በማርከስ ነውረኛነታቸውን አሳይተዋል።

ሰዎችንም በመግደል በመኖሪያ ቤትና በማሳ በመቅበር ከሰብአዊነት ያፈነገጠ ተግባር አከናውነዋል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎችም ከአሸባሪዎቹ ሸኔና አልሻባብ ጋር በማበርም ንጹሃንን ጭካኔ በተሞላበት መልኩ እንዲታረዱ አድርገዋል። ጨቅላ ሕፃናት ሳይቀሩ በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ፈርደዋል።

የትህነግ የሽብር ብድን ቆሜለታለሁ ለሚለውም የትግራይ ሕዝብ የሚራራ አይደለም። ሕፃናትን በሀሽሽ አደንዝዞ በጦርነት ከማሰለፍ ባሻገር የእናቶች ዘመቻ በሚል ወላዶች የጦርነቱ ሰለባ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ወላጆች ልጆቻችን የት ደረሱ የሚል ጥያቄ እንዳያነሱ በርካታ ልጆች በጦርነቱ የሞቱባቸውን በመለየት «የእናቶች ዘመቻ» በሚል በግንባር ለጦርነት ግዳጅ አሰልፏቸዋል።

በአግባቡ ያልሰለጠኑ ሕፃናትን በግዳጅ በማሰለፍ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ ሰራዊት ፊት እንዲቆሙ ከማስገደዱም ባሻገር ፈርተው የሚሸሹትን ከኋላቸው በጥይት እንዲደበደቡ ትዕዛዝ እስከመስጠት ድረስ የዘለቀ አረመኔያዊ ድርጊት የሚፈጽም ግፈኛ ቡድን ነው። ሰሞኑንም ተጠልፎ የወጣ የድምጽ መረጃ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው።

ይህ አረመኔ ቡድን የሕዝብ ማዕበል የሚል ኋላ ቀር የጦርነት ስልት በመከተል ሕፃናትንና አረጋውያንን ጭምር በጦርነት ጭዳ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህም ሳያንሰው በጦርነቱ አካላቸውን ያጡ ሕፃናትን ደብቆ በማስቀመጥ ከሕዝብ እንዳይደባለቁ መድሎ በማድረግ ላይ ነው።

የትህነግ የሽብር ቡድን ርሃብን እንደፖለቲካ የሚጠቀምና በሕዝብ ዕልቂት የፖለቲካ ጥቅም እስካገኘ ድረስ ማንኛውንም ተግባር ከመፈጸም ወደ ኋላ የማይል ነው። በተለይም የሰብአዊ ድጋፎችና የእርዳታ እህልን ከተራቡ ጉሮሮዎች በመንጠቅ ህልውናውን የማቆየት ባህል አለው። በ1977 በተከሰተው ርሃብ ለትግራይ ሕዝብ የተላከውን ስንዴ በመሸጥ ለጦር መሣሪያ መግዣ አውሎታል። በዚህም የሚበሉት አጥተው በርካቶች በርሃብ እንዲረግፉ ምክንያት ሆኗል።

ሰሞኑንም መቀሌ ከሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መጋዘን ከግማሽ ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ በመስረቅ የእርዳታ እህል ለሕዝብ እንዳይደርስ የተለመደ ክህደቱን ፈጽሟል። በተመሳሳይም የሕፃናትን አልሚ ምግብ በመስረቅ ለታጣቂዎቹ እንደሚያውል ቡድኑ በኃይል ከለቀቃቸው ምሽጎች ውስጥ ማስረጃዎች መገኘታቸው የሚታወቅ ነው። የቡድኑ ከትናንት እስከ ዛሬ የጭካኔ ጥግ እንዘርዝር ካልን በዚህ ጽሑፍ የሚያልቅ ሳይሆን ታሪክ በስፋት የሚዘግበው ይሆናል።

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የልቦና ውቅራችን አብሮ ይታደስ

ለውጡ እስከ ባዕተበት መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ያልዘመመ እና ውሀ ልኩን ያልሳተ የልቦና ውቅር አልነበረም። የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ ወዘተርፈ የልቦና ውቅራችን ዘሞ ነበር ማለት ይቻላል። ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ የተቀነቀነው የማንነትና የዘውግ ፖለቲካ የዘመመ የልቦና ውቅር አዋቅሯል። በዚህ የተነሳም በዜጎቿ መካከል ጥላቻ፣ ልዩነትና መጠራጠር በመጎንቆሉ ላለፉት ጥቂት አመታት ሁላችንንም ያሸማቀቁ፣ አንገታችንን ያስደፉና ያሳፈሩ፤ ለማየት የሚዘገንኑ ለመስማት የሚሰቀጥጡ ጥቃቶችና ግፎች ተፈፅመዋል።

98 በመቶ የሚሆን ዜጋ የተለያዩ ዕምነቶች ተከታይ በሆነባት ሀገር የቻርለስ ዳርዊን ዝግመት ለውጥ አማንያን፤ ፈጣሪ የለም በሚሉ ጉግ ማንጉጎች ማለትም በእነ ማርክስ፣ ኤንግልስ፣ ሌኒን፣ ስታሊን፣ ማኦ፣ ፓል ፓት፣ ወዘተረፈ የተተወረ የሶሻሊስት ርዕዮተ አለም (አይዶሎጂ) ተከታይ የሆን ጊዜ የልቦና ውቅራችን ዘሟል። ከኢትዮጵያውያን የስነ ልቦና ውቅር የተናጠበ የግማሽ ክፍለ ዘመን ማህበራዊ ወረታችንን፣ እሴታችንንና ትውልዶች ከማሳጣቱ ባሻገር የከሸፉ ሁለት አብዮቶችን አስታቅፎን፤ ዛሬ ድረስ የራስ ምታት ታማሚ ላደረገን ፖለቲካዊ ሀንጎቨር አሳልፎ ሰጥቶናል።

ሀገራችን ለ50ና ከዚያ በላይ አመታት በድቅድቅ ጨለማ እንድትደናበር አድርጓል። ይህ ብቻ አይደለም ህልመኛና ሀገር ወዳድ የሆነ ትውልድ አሳጥቶናል። የትውልድ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል። ለብልፅግና መሰረት የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዳንገነባ፤ ተቋማትን እንዳንከተል አድርጎናል። በተለይ በዘመነ ትህነግ/ኢህአዴግ ተጠያቂነት ባለመኖሩ ሀገር በጠራራ ስትዘረፍ ፤ የዜጎች መብት በአደባባይ ሲጣስ በመኖሩ ዛሬ ለምንገኝበት ፈተና ዳርጎናል። ዳፋው ገና ለአመታት እንደ ጥላ ይከተለናል።

ከ50 አመታት በላይ እየተፈራረቀ ተጭኖብን የኖረው የሶሻሊስትና የማንነት ፖለቲካ እንደ ሀገርም እንደ ሕዝብም የልቦና ውቅራችንን ከመሰረቱ አናግቶታል። አዛብቶታል። በተለይ የሶሻሊዝም አይዶሎጂ የሃይማኖት ተቋማትን አዳክሟል። የሀይማኖት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን ሆን ብሎ ማህበራዊ ቦታቸውን እንዲያጡ አድርጓል። ከፈጣሪያቸው ይልቅ እነ ማርክስን እንዲያመልኩ እስከ ማስገደድ ደርሶ ነበር። እንደ ባህላዊ ሽምግልና፣ ገዳ ያሉ እሴቶች እንዲደበዝዙ ፤ ለዘመናት አጋምደው በአብሮነት ያኖሩን ዘመን ተሻጋሪ ባህላዊ ትስስሮችን አንድ በአንድ አቋርጧቸዋል።

በዚህም ለባህሉ ለእሴቱ ግድ የማይለው ትውልድ ተፈጥሯል። ታላላቆቹን የሚያንጓጥጥ፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና የሃይማኖት አባቶቹን ቁልቁል የሚያይ ትውልድ መጥቷል። በአናቱ ለአመታት ሲነዛና ሲቀነቀን የነበረው የተዛባ የማንነት ፖለቲካ ሲጨመር፤ "ኢትዮጵያ ትውደም!" የሚል፤ በየቀዬው የተፈጥሮ ሀብት ብሔርተኝነትን በመፍጠር ዜጋን በማንነቱ የሚነቅል የሚያፈናቅል ጽንፈኛ ትውልድ ተፈጥሯል። በሀገሪቱ እዚህም እዚያም ጥላቻና ቂም ተንሰራፍቷል። የጋራ ታሪክና ጀግና ከመቀዳጀት ይልቅ በፈጠራ ትርክት እየተጓተተ ይገኛል።

በሶሻሊዝምና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲንጠራወዝ የኖረው የኢኮኖሚ መዋቅር ድህነትን፣ ኋላቀርነትን፣ ስራ አጥነትን፣ የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ግሽበትን አስታቅፎ ጥቂት ባለጊዜዎችን ደግሞ ባለጠጋ አድርጎ እንደ ደራሽ ጎርፍ አልፏል። ይህም ኢ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ፈጥሯል። በዚህ የተነሳ ወጣቱ በትንሹም በትልቁም ሆድ እንዲብሰው ከማድረግ አልፎ ለተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች መጠቀሚያ ሆኗል። ሀገርም ሕዝብም ለጉስቁልና ተዳርጓል። በዚህ አጭር መጣጥፍ የዘመሙ የልቦና ውቅሮች ያስከተሉትን ዳፋ ፤ እያስከፈሉን ያለውን ውድ ዋጋ ሁሉ ማውሳት አይቻልም። ይሁንና የዘመሙ የልቦና መዋቅሮች ለማቃናት የለውጥ ኃይሉ በተለይ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ አንዳንድ ሚዲያዎችና እንደ ዶ/ር ምህረት ደበበ ያሉ ሀገር ወዳድ ዜጎች ጥረት እያደረጉ ቢሆንም የዘመሙ የልቦና ውቅሮች የትየለሌና ለዘመናት ሲንከባለሉ የኖሩ ስለሆኑ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ መሆን አልተቻለም።

**የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘብ የነበሩት የደህንነት የጸጥታና የሰላም ተቋማት በተደረገ ማሻሻያ ከፓርቲ ቃፊርነት ወጥተው የሕገ መንግስቱ የሀገርና የሕዝብ ምሽግ ሆኑ። የመከላከያ ሰራዊት ከአንድ ፓርቲ መሳሪያነት ወጥቶ አራት አመት ባልሞላ ጊዜ እጅን በአፍ የሚያስጭን አንጸባራቂ ድል በማስገንዘብ የሀገርን ህልውና ያስቀጠለው እያስቀጠለ ያለው የዘመመው የልቦና ውቅር ማለትም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘብነቱ ወደ ሕገ መንግስት የመጨረሻ ምሽግነት ቀና በማለቱ ነው**

በነገራችን ላይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግስት እየወሰዳቸው ያሉ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች ማለትም የኢትዮ ኤርትራ የሰላም ስምምነት፣ የተቋማት ግንባታ፣ የመደመር ጽንሰ ሀሳብ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ አረንጓዴ አሻራ፣ ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት፣ የእንጦጦ ፓርክ ልማት፣ የቤተ መንግስት ልማት፣ ከሸገር ወደ ሀገር፣ የአረጋውያን ቤት ጥገና፣ ችግኝ መትከልና ውሃ ማጠጣት፣ ከተማ ማፅዳት ለአካል ጉዳተኞችና ለችግረኞች የሚደረግ እርዳታ፣ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚያደርጓቸው ተከታታይ ውይይቶች፣ በየበዓላት የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች፣ በፌስ ቡክ ገጻቸው የሚያወጧቸው ጹሑፎች፣ የቀዳማዊ እመቤት የትምህርት ቤት ግንባታዎች፣ ወዘተረፈ የዘመሙ የልቦና ውቅሮች ለማቃናት የሚካሄዱ ወካይ/ ሲምቦሊክ / ጥረቶች ናቸው።

እነዚህ ወካይ ጥረቶች እንዲሰፉና እንዲጠልቁ ግን ተቋማዊ የማድረጉ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ሌላው ሊጤን የሚገባው ጉዳይ የዘመሙ የልቦና ውቅሮች በአንድ ግለሰብ ወይም በለውጥ ኃይሉ ጥረት ብቻ የሚቃኑ ስላልሆኑ በአዲሱ አመት የራሳችንን፣ የማህበረሰባችንን፣ የምንሰራበትን ተቋም፣ የሀገራችንና የሕዝባችንን የዘመመ የልቦና ውቅር ለማቃናት እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንተጋ ቃል እንግባ። ቃላችን እናድስ። የሀገሪቱን የዜጋውን የተቋማቱን የተዛመሙ የልቦና ውቅሮች ቀና ለማድረግ የተቋማት ግንባታ ወሳኝ ሚና አለው።

የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መሠረተ ልማት ወይም ተቋማት ማለትም ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ብዙኃን መገናኛ፣ የሰብዓዊ መብት እና የእንባ ጠባቂ ኮሚሽን፤ የፍትሕ፣ የዳኝነት፣ የጸጥታ፣ የደህንነት፣ የትምህርትና ሌሎች ተቋማት ግንባታ እየተካሄደ ነው። በዚህም በዚያም የዘመመውን የልቦና ውቅር ለማቃናት ጥረት ተጀምሯል። ለውጡን ተቋማዊ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ተስፋ ሰጪ ጅምር ስራዎችም ይበል የሚያስብሉ ናቸው። ተቋማቱን ከሞላ ጎደል ገለልተኛ ለማድረግ የሚያግዙ ማሻሻያ እርምጃዎችም ውጤት ማሳየት ጀምረዋል። የዳኝነት አካሉን፣ ምርጫ ቦርድን፣ ሚዲያውንና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማትን ነፃና ገለልተኛ ለማድረግም በአሰራርና በአደረጃጀት የታገዙ ለውጦች እየተተገበሩ ይገኛል።

ከለውጡ በፊት የነበረው አገዛዝ ለጭቆና ለአፈና ይጠቀምባቸው የነበሩ አዋጆች ተሻሽለዋል። በመሻሻል ላይም ናቸው። አዳዲስ አዋጆችና ሕጎችም በሒደት ላይ ይገኛሉ። ተቋማዊ የግንባታ ሂደቱን የሚያግዙ በርካታ አዋጆችና ውሳኔዎች ፀድቀው ስራ ላይ ውለዋል። ከፀደቁት መካከል የምርጫ ቦርድ የማቋቋሚያ እና የሲቪል ማህበራት አዋጆች ይገኙበታል። ለሽግግር ሂደቱ አጋዥ ከሆኑ ውሳኔዎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ፣ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ክብርት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ዳንኤል በቀለ (ፒኤችዲ) እና የመንግስት መገናኛ ብዙኃን የስራ አመራር ቦርድ አባላት ምደባን በአብነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሹመቶች መንግስት ነፃና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማትን በመገንባት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

ከአራት አመታት በፊት በተለያዩ ወንጀሎች ተፈርጀው እና የፖለቲካ ምህዳሩ በመከርቸሙ በእስር፣ በስደትና በትጥቅ ትግል ለነበሩ ዜጎች፣ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ይቅርታና ምህረት የተደረገው የዘመመውን የልቦና ውቅር ቀና ለማድረግ ነው። እንዳርጋቸውን፣ አንዷለምን፣ እስክንድርን፣ ተመስገን፣ እማዋይሽን፣ ንግስትን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞች ተፈተዋል።

አርበኞች ግንቦት 7፣ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር እና የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር የፖለቲካ ድርጅቶች በምህረትና በይቅርታ ወደ ሀገር ተመልሰው ሰላማዊ ትግሉን ተቀላቅለዋል። እንደ ኢሳት ያሉ ከ200 በላይ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ድረ ገጾች፣ ጦማሮች፣ ጋዜጦችና መፅሔቶች እንደገና ወደ ስራ ተመልሰዋል። ፍትሕን፣ ኢትዮጲስን፣ ዘሀበሻን፣ ሳተናውን ለአብነት ማንሳት ይቻላል። የዘመመው የሀገር የሕዝብና የመንግስት የልቦና ውቅር ቀና የሚለው በአንድ ጀምበር ባይሆንም አበረታች ለውጦች መታየት ጀምረዋል።

አምስት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመከላከያና በሌሎች የጸጥታና የደህንነት ተቋማት ፤ በየኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ፤ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ በብዙኃን መገናኛ፣ በሶስቱ የመንግስት አካላት ማለትም በሕግ አውጪው ተርጓሚውና አስፈጻሚው ለአመታት ይስተዋል የነበረውን መደበላለቅ በአሰራርና በአደረጃጀት ለመለየት የተጀመሩ ጥረቶች የዘመመውን የልቦና ውቅር ለማቃናት ለሚደረገው ጥረት እሴት ጨምረዋል።

## እንደ መውጫ

በአዲሱ አመት የዘመሙ የልቦና ውቅሮችን የማቀናቱ ጥረት መቀጠል አለበት። መንግስት ለውጡን ተቋማዊ የማድረግ ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥል። ዜጋ ተቋማቱ ውጤታማ እንዲሆኑ የድርሻውን ይወጣ። ተቋማት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጡ። የለውጥ ኃይሉ ምርጫ ቦርድ ነጻ ገለልተኛና ተአማኒ እንዲሆን የሄደበትን ርቀት ልብ ይሏል። ሕግ አሻሻለ፣ ክብርት ብርቱካን ሚደቅሳን ሰብሳቢ አደረገ። የቦርዱን ውሳኔ ያለምንም ማቅማማት ተቀበለ። በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ በዜጋው ተአማኒ የሆነና ተቀባይነት ያለው ተቋም በመሆኑ ዘመም የነበረው ነጻ ተአማኒና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የማካሄድ የልቦና ውቅር ቀና ማለት መጀመሩን በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ አረጋገጠልን።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘብ የነበሩት የደህንነት የጸጥታና የሰላም ተቋማት በተደረገ ማሻሻያ ከፓርቲ ቃፊርነት ወጥተው የሕገ መንግስቱ የሀገርና የሕዝብ ምሽግ ሆኑ። የመከላከያ ሰራዊት ከአንድ ፓርቲ መሳሪያነት ወጥቶ አራት አመት ባልሞላ ጊዜ እጅን በአፍ የሚያስጭን አንጸባራቂ ድል በማስገንዘብ የሀገርን ህልውና ያስቀጠለው እያስቀጠለ ያለው የዘመመው የልቦና ውቅር ማለትም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘብነቱ ወደ ሕገ መንግስት የመጨረሻ ምሽግነት ቀና በማለቱ ነው። በፍትሕ መዋቅሩ በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ፤ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት የተደረጉ ማሻሻያዎች ያመጡት የልቦና ውቅር ለውጦች ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው።

የተፈጠረው ሀገራዊ አንድነትና መተሳሰብ የልቦና ውቅር ለውጡ ትሩፋቶች ናቸው። ለ27 አመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆነው የተሰራባቸው የጥላቻ የልዩነት የቂም በቀል የሁከት የሀሰተኛ ትርክት የስግብግብነት የውሸት የአቅላይነት የሌብነት የመጠላለፍና የሴራ ፖለቲካ ወዘተረፈ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መዋቅራዊና ተቋማዊ መሆናቸው ስለቀረ እንደ ኩይሳ በቁማቸው እየፈረሱ ቢሆኑም በአዲሱ አመት የቀሩትን የልቦና ውቅሮች በማቃናት ፍቅር፣ ሰላም፣አንድነት፣ ይቅር ባይነት እርቅ፣ መነጋገር፣ መደማመጥ፣ መቀባበል ወዘተረፈን ቤተኛ ለማድረግ እንደ ካችአምናው ሌት ተቀን እንስራ። ተቋሞቻችንን እንጠብቅ። እናከብር፣የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ቤተመቅደሶች ናቸውና።

**አዲሱ አመት የሰላም፣ የጤና፣ የብልፅግና እና የአንድነት ይሁን !!!**

**አሜን።**

# ወቅታዊ

# “ለሸፈተ ሽፍታ፣ ህግ አላከብርም ለሚል ቡድን መንግስት ህግ የማስከበር ኃላፊነት አለበት”

- አቶ ኪዳነማርያም ጸጋዬ

መሰረት ገ/ዮሐንስ

**ውልደታቸውና እድገታቸው በአክሱም ከተማ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአክሱም ሁለተኛ ደረጃ በመቐለ ከተማ ፀሀይ ዮሃንስ ትምህርት ቤቶች ተምረዋል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። አሁን የሚኖሩት በአሜሪካ ሀገር ነው። የዛሬው እንግዳችን አቶ ኪዳነማርያም ጸጋዬ።**

**አቶ ኪዳነማርያም ወደ ፖለቲካ የገቡት፤ በወጣትነት ዘመናቸው ትግራይ ከሚል ስሜታዊነት በመነሳት አሁን የቡድኑ መሪዎች ከሆኑት ግለሰቦች ጋር በመሆን ነበር። ቡድኑ በወቅቱ ይከተለው የነበረው የፖለቲካ አካሄድ ትክክል ስላልነበረ ብዙም ሳይቆዩ ቡድኑን ተለያይተዋል። ለዚህም ምክንያታቸው €€ብሄር የሚል አካሄዳ ነበር ፣ ይህ ደግሞ አልገባኝም በወላጆቻችን ያልነበረና በአጠቃላይ ዓላማው ትክክል ስላልሆነ ነው‹‹ ሲሉ ይገልጻሉ።**

**ቡድኑ ከውልደቱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የትግራይን ህዝብ ጨምሮ ሀገርን በጦርነት እያማረረ ነው። መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ቡድን ማስወገድ አለበት የሚል ሃሳብ አላቸው። ከላይ የተጠቃቀሱትንና ሌሎች ሃሳቦችን በማንሳት ከአቶ ኪዳነማርያም ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ!**



**አዲስ ዘመን፡- የፖለቲካ ተሳትፎ የጀመሩት መቼ ነበር ? በምን ምክንያት ነበር የገቡት ?እስካሁንስ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ያልዘለቁበት ምክንያት ምን ነበር ?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ድሮ ወጣቶች እያለን ማለትም በመቐለ ከተማ ፀሀይ ዮሃንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተማርን እያለን ‹‹ትግራይ›› የሚል ስሜታዊ የሆነ ንቅናቄ ተጀምሮ ነበር። በዛን ሰዓት አሁን ካሉት የሕወሓት መሪዎች ጋር አብረን ነበር ስንማር የነበረው። ያን ጊዜ እውቅናም አልነበረንም ፤ እነሱ የህዝብ ብሄራዊ እንቅስቃሴ የሚሉት እና ዓላማ አድርገው የገቡበት ብሄር ተኮር ፖለቲካ መሆኑ በዛን ሰዓት አናውቅም ነበር፤ ግን ገብተንበት ነበር። ሆኖም ነገሩ ቆይቶ ስለገባኝ ብዙም አልቆየሁም፤ በአጭር ጊዜ ከቡድኑ ጋር የነበረኝን ግንኙነት አቆምኩ።

የቡድኑን ሀሳብ ያልተቀበልኩት ብሄር የሚባል ነገር ለኔ አይገባኝም ነበር። በዛን ሰዓት ልጆች ስለነበርን ብዙ ነገር በስሜት ብቻ እንጓዝ ነበር። ለዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ እንድናደርግ ያደረጉን ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ይሰጥ የነበረው ናሽናል ሰርቪስ / ብሄራዊ ግልጋሎት/ ነው። በበወቅቱ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ሶስት አመት ከተማሩ በኋላ ወደ አራተኛ አመት ከመግባታቸው በፊት በየሙያቸው እንዲያገለግሉ ለአንድ አመት ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይበተኑ ነበር።

እኛንም ወደዚህ ስሜት እንድንገባ የገፉፉን ወደ መቐለ ተመደበው የመጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸው። አሁን ያሉት የአሸባሪው ሕወሓት መሪዎች በዛን ሰዓት ልጆች ነበሩ፤ ትላልቆቹ እኛ አናውቃቸውም ነበር። ቀጥሎ እነ ስብሀት ነጋ ፣ እነ ገብረኪዳን ደስታ ፣ አበበ ተሰማ የሚባሉት ብሄር የሚል በወላጆቻችን ያልነበረ ነገር ያንፀባርቁ ነበር። በዚህ ጊዜ ሁኔታውን በራሴ መመራመር ጀመርኩ። ትክክል አለመሆኔ ሲገባኝ ከዚያ እንቅስቃሴ ራሴን ማግለል ችያለሁ። በዛን ሰዓት ብዙ ስሜታዊ የሚያደርጉ እና መሰረት የሌላቸው ነገሮች እኔን ጨምሮ ብዙ ወጣቶች ወደ እንቅስቃሴ እንዲገቡ አድርጎን ነበር።

**አዲስ ዘመን ፡- የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን አሁን ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት መጀመሩን እና አሁን ትግራይ ላይ ያለውን ሁኔታ እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ኪዳነማርያም ፡-** በለውጡ ማግስት አሸባሪውን ሕወሓት ጨምሮ ሁሉም የተማረ የሚባለው ኃይል ሳይቀር ከአዲስ አበባ አኩርፎ ነው ወደ መቐለ የሄደው። በፖለቲካ ዓለም እንዲህ አይነት አይተን አናውቅም። ለዚህ ምንም ምክንያት የላቸውም። 27 ዓመት ኢትዮጵያን ሲገዙ ሁሉም ዝም ብሎ ነበር የተገዛላቸው። የኢትዮጵያን መንግስት እንደ መንግስታቸው ተቀብለው ነበር የሚኖሩት፤ አሁን የለውጥ መንገድ በኢትዮጵያ ሲመጣ ወደ ትግራይ በመሄድ ‹‹ትግራይ ትግራይ›› ማለት ትርጉም የለውም። እነሱ ያመጡት ህገ መንግስት እኮ ነው ያለው። ትግራይን ከፍሎ የገዛ ሰው የለም ፣ በየክልሉ ራስህን ነው የምታስተዳድረው ብለው ህጉን ያወጡት እራሳቸው ናቸው።

ጦርነቱን እራሳቸው ከጀመሩ በኋላ ‹‹ሊያጠፉን ፈልገዋል›› በሚል መጮህ ቀጠሉ። ይህን ጦርነት እኮ ከመጀመሪያው ያስጀመሩት እራሳቸው ናቸው። ቀድመው ተዘጋጅተው ‹‹እናሸንፋለን ፣ ሕወሓትን የሚያሸንፈው የለም ›› በሚል ነው ወደ ጦርነት የገቡት። ይህ ሊሆንላቸው አልቻለም። በራሳቸው ምክንያት ነው በጠላት የተከበቡት። ለሃያ ሰባት አመታት መንግስት በነበሩበት ሰዓት እኮ የትግራይ ህዝብ ከጎናቸው ነበር፤ ይህ መንግስት የኛ ነው በማለት ለአባይ ብር አዋጥተዋል። ድሮም ከነሱ ጎን ነበር። እነሱ ናቸው ያላስታወሱት እንጂ።

አሁን ያለው ማኩረፍ ኢትዮጵያን ለመግዛት ባለመቻላቸው የመጣ ኩርፍያ ነው። የሕወሓት አመራሮች ብቻ አይደለም፤ ሁሉም ሰው ከጠላ ቤት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ በዚህ ስሜት ገብተው እየተዋጉ ነው። ይህ እብደት ነው። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ነች። ትግራይ የምትባለዋን መሬት የትግሬዎች ብቻ መሬት አይደለችም የኢትዮጵያ ጭምር ነች። ማንም ኢትዮጵያዊ ትግራይ እንድትገነጠል አይፈቅድም። አሁን በትግራይ እየሆነ ያለው ለከንቱ አላማ የሚከፈል ከንቱ ዋጋ ነው። ማርከናል ፤ገድለናል ሊሉ ይችላሉ መጨረሻው ግን የማይሆን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ለሰላም እና ለድርድር የሰጠውን እድል ቡድኑ ለምን አሻፈረኝ ብሎ ጦርነትን መረጠ ?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ሲጀመር ከዚህ ቡድን ጋር ድርድር የሚባል ነገር ያስፈልጋል የሚል እምነት የለኝም። ከቡድኑ ጋር መደራደር አሳፋሪ ነው እላለሁ። መንግስት ከአንድ ከሸፈተ ሽፍታ ቡድን ጋር ድርድር ብሎ መናገሩ ለራሱ በጣም የሚያሳፍር ነው/ ጉዳዩ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ቢሆንም/ ፌደራል መንግስት ችግሩን በሀይል መቀልበስ አለበት። ህጋዊ ያልሆነን አካል ህግ ማስከበር አለበት። ለዚህ ሲባል የሚያካሄደው ጦርነት ህግ ማስከበር ተብሎ ይጠራል።

ስለ ሰላም ለማውራት እኮ መሳሪያ መውረድ አለበት። መሳሪያ ተሸክመህ ሰላም የሚባል ነገር የለም። እነሱ መሳሪያቸውን አያወርዱም ፣ በዚህ የሚታለል ሰው የለም። ስለዚህ ያለው አማራጭ መንግስት ከህዝብ ጋር በመተባበር ህግ ማስከበር ነው።

የሰላም ውይይት ሲባል እኔ በግሌ ከመጀመሪያ ጀምሮ አልተቀበልኩትም። የዓለም ማህበረሰብ እንዲያውቀው ከሆነ አላውቅም ለኔ ግን መሳሪያ የማያወርድ ሀይል ሰላም ማምጣት አይችልም። መሳሪያቸውን ካወረዱ እኮ ሌላው ነገር ቀላል ነው። አሉ የሚባሉ ችግሮች ወደ ጦርነት የሚያስገባ አይደሉም፣ ዋናው ጉዳይ መሆን ያለበት ይሄ ቡድን መሳሪያ ያወርዳል ወይ የሚለው ነው መሆን ያለበት።

ብዙ ሰው ስሜታዊ ሆኖ እነሱን ተከትሎ እየሄደ ነው። ከአሸባሪው ሕወሓት አመራር ባለፈ ቀደም ሲል እንዳልኩት ከጠላ ቤት እስከ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ሊዋጋ የወጣ ሰው ነው ያለው። እስከ መጨረሻ ሊዋጉ ነው። ምክንያቱም ጦርነቱን ጀምረውታል። ያሰቡት ነገር ካልተሳካላቸው ጥያቄ ሊመጣባቸው ነው፣

ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሄው ያለው በፌደራል መንግስት እጅ ነው። ከሕወሓት የሚመጣ የተለየ ሃሳብ አለ ብዬ አልገምትም። እነሱ እኮ ግድ የላቸውም፣ ይህ ሁሉ ሰው በጦርነት እየሞተ ነው ፣ ይህ ሁሉ ህጻን ወደ ጦርነት እየሄደ ነው፣ ይህን ሁሉ አድርገው መጨረሻቸው ምንድነው የሚሆኑት? ይህን ሁሉ አድርገው ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያን መምራት አይችሉም

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



**ይህ ህዝብ ሰላም ማግኘት አለበት፤ ደክሞታል። በጦርነት ምክንያት የትግራይ ህዝብ ብቻ አይደለም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው የሰለቸው። በግርግር የሚሆን ነገር ፤የሚመጣም ሰላም የለም። ሰላም ከማይፈልግ ፍጥረት እንዴት ነው ሰላም የሚመጣው? አሜሪካና አውሮፓ ሰላም ስላሉ የሚመጣ ሰላም የለም። እነሱ እዚህ ጋር ግድ የላቸውም። እነሱ በየትኛውም ዓለም ሰላም አድርጉ እያሉ ነው የሚናገሩት። እቺ ሰላም እንዴት አድርጋ ትምጣ? ነው ትልቁ ጥያቄ**

ስለዚህ እስከ መጨረሻ መሄዳቸው አይቀርም። መሳሪያቸውን እስካላወረዱ ድረስ ሰላም ማምጣት አይቻልም።

የሕወሓት ቡድን ባህሪ እና አመጣጡ በጦርነት ነው፤ አሁንም ለእዚህ እኮ ነው ጦርነቱን የጀመሩት። አሁን ግን ከዚህ ነገር የሚወጡበት መንገድ የለም። መውጫ ስለሌላቸው እስከ መጨረሻ ተዋግተው መሞት ይመርጣሉ። መንግስት በትግራይ አፍኙ እይዛቸዋለሁ ብሎ ካሰበ እነሱ አርፈው አይቀመጡም ጅሎች አይደሉም። ስለዚህ አማራጭ የሚሆነው ይህንን ጦርነት ወደ ፍጻሜ ማድረስ ነው። ቡድኑን በሀይል ማስወገድ ነው። የሰላም ውይይት የሚባለውን ነገር ከእነሱ የቆየ ባህሪ አንጻር መቀበል ይከብዳል።

ቡድኑ ከድሮም ጀምሮ ስለ ሰላም ሆነ የሰላም ታሪክ የለውም፤ ለዚህ ነው ጦርነቱን እራሳቸው የጀመሩት። ይሄንን ያደረጉትም ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ነው፣ እጃቸውን መስጠት አይችሉም። ስለዚህ መንግስት ሀይሉን ማጠናከር ነው ያለበት። ከመቶ ሚሊየን በላይ ህዝብ የሚወክል መንግስት እንዴት አድርጎ ነው ህግ ማስከበር የሚያቅተው ? ይህ ለኔ ጥያቄ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመቀሌ የሚገኘው የዓለም ምግብ ፕሮግራም ከግማሽ ሚሊየን በላይ ሊትር ነዳጅ አሸባሪው ሕወሓት እንደዘረፈው ገልጾ ነበር ፣ በዚህ ላይ ያሉት አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ይህ እኮ የሚደንቅ ነገር አይደለም። እነሱ ሽፈታ ናቸው። ስራቸው የሽፍታ ስራ ነው፤ ስለዚህ ምንም ግድ የላቸውም። ለእነሱ ተሰጥቶ ቢሆንስ? በስም የትግራይ ህዝብ ድጋፍ ተብሎ ለነሱ ተሰጥቶ ቢሆንስ ? ለምንድነው ይህ ሁሉ ነዳጅ የሄደው ፣ ይህ ሁሉ ነዳጅ በስም ድጋፍ ተብሎ ነው የሄደው። ለአንድ ቀን ወሰዱት ሰረቁት ከተባለ በኋላ ከዛ በኋላ ምንም የተባለ ነገር የለም፣ ዝም ዝም ነው። ሲቀጥል ግን እነዚህ ሽፍቶች ስለሆኑ ቢሰርቁም፤ ቢዘርፉም የሚደንቅ አይደለም። የሽፍታ ስራ እኮ መዝረፍ ፣ መግደል፣ ማሳደድ ነው፤ ስለዚህ የሰሩት ስራ አዲስ ነገር አይደለም። የለመዱት የነበረ ባህሪያቸው መገለጫ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገር ሰላም እንዲሆን የትግራይ ዲያስፖራ አስተዋጽኦ ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** በውጭ የሚገኙት የትግራይ ተወላጆች ልክ ሀገር ውስጥ ካሉ የትግራይ ተወላጆች ጋር አንድ ናቸው። ለምሳሌ እኔ ባለሁበት ከተማ እኔ ብቻ ነኝ የተለየ ሃሳብ ያለኝ። አብዛኛው የትግራይ ተወላጅ የነሱ ደጋፊ፤ የነሱ አጨብጫቢ ነው። እዚያ ያለውም የትግራይ ተወላጅ ልክ ሀገር ውስጥ እንዳለው የትግራይ ተወላጅ ስሜታዊ ነው። ትግራይ ሀገር ትሆናለች ብለው ያስባሉ፤ ወይም እንድትሆን ይመኛሉ። ሀገር የማድረግ የእብደት ህልም አላቸው፣ በዚህ ስሜት ውስጥ ነው ያሉት።

እየወጡ መንገድ ላይ እየወደቁ እና ሰልፍ እያካሄዱ እዚህ ላለው መንግስት እያሳዩ ነው የሚውሉት። አሁን ግን ደከማቸው መሰለኝ እያየኋቸው አይደለም። አዲስ አበባም እኮ ብዙ ደጋፊ አላቸው። ልዩነቱ ውጪ ሀገር ትንሽ ነጻነት አላቸው፤ አዲስ አበባ እኮ አንድ ጀነራል ሲሞት ‹‹ትግራይ ትስዕር ›› አላሉም እንዴ? መቃብሩ ላይ ሂደው። ‹‹ትግራይ ትስዕር›› ብለዋል እኮ! መንገድ አገኘን ብለው። በውጭ ሀገርም እንደዚህ ያለ ሃሳብ ነው ያለው።

ለዚህ ሁሉ መፍትሄው ያለው በፌደራል መንግስት እጅ ነው። ከእነሱ የሚመጣ የተለየ ሃሳብ አለ ብዬ አልገምትም። እነሱ እኮ ግድ የላቸውም፣ ይህ ሁሉ ሰው በጦርነት እየሞተ ነው፤ ይህ ሁሉ ህጻን ወደ ጦርነት እየሄደ ነው፤ ይህን ሁሉ አድርገው መጨረሻቸው ምንድነው የሚሆኑት? ይህን ሁሉ አድርገው ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያን መምራት አይችሉም።

ግልጽ ለመናገር ትግራይ የኢትዮጵያ እንጂ የትግሬዎች ብቻ አይደለችም። የሆነ የኢትዮጵያ ቦታ የኢትጵያውያን ነው። ይህ ሚስጥር ነው ያልገባቸው። ኤርትራን ራሳቸው ናቸው የገነጠሏት። በነሱ ጊዜ ስለተገነጠለች አሁንም የሚሆንላቸው መስሏቸው ነው ይህን የሚያደርጉት፤ ትግራይን መገንጠል ነው አላማቸው። ይህን ዓላማ ይዘው ነው እየተጓዙ ያሉት። እዚህ ጋ ድብብቆሽ የለም። ዲያስፖራውን የሚወስነው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉ ጉዳዮች ናቸው። መንግስት ያለውን ሀይል ተጠቅሞ የሚደረገውን ካደረገ የእነሱ መንጫጫት ምንም የሚያመጣው ነገር የለም።

**አዲስ ዘመን፡- በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ይሄ ጉዳይ ጉዳዩ አይደለም። ሲጀመር ሁሉም አፍሪካ ሀገራት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ናቸው። በአፍሪካ አንዲት ሀገር ችግር ሲገጥማት ሁሉ የአፍሪካ ሀገራት ነው የሚመለከታቸው።

የአፍሪካ ህብረትን ጥሶ በኢትዮጵያ ላይ አደጋ ማድረስ የሚችል ሀይል ይሁን መንግስት በዓለም የለም። ፖለቲካው ይህ ነው። ማንም አፍሪካ ህብረት ሳይፈቅድ በአንዲት አፍሪካ ሀገር አንድ ችግር መፍጠር ማለት ከመላ አፍሪካ መጣላት ማለት ነው። ስለዚህ ይህን ያውቃሉ፣ ግን አንድ ነገር ማድረግ አልቻሉም። ሆኖም ግን አሜሪካና አውሮፓ እንዲህ ሊያደርጉልን ነው ሲባል ነው የሚሰማው።

አሜሪካ የኢትዮጵያ ጠላት አይደለችም። ከክሊንተን ጀምሮ ሕወሓት ሃያ ሰባት ዓመት ሲመራ የኑሱ ደጋፊዎችን፣ በነሱ የበሉና የጠጡ ናቸው ለአጭር ጊዜ ጫና የፈጠሩት። የዓለም ማህበረሰብ የሚባል ነገር የለም፡ ሲጀመር ኢትዮጵያ የዩናይትድ ኔሽን አባል ናት። በአንዲት ሀገር የውስጥ ጉዳይ ማንም ጣልቃ አይገባም። እነሱ መግባት የፈለጉት በጀኖሳይድ ነው። ይህ ደግሞ ጀኖሳይድ አልተፈፀመም ተባለ ስለዚህ በምን ይግቡ። ጀኖሳይድ ከተፈፀመ ይገባሉ፤ ከሩዋንዳ በኋላ የተፈጠረ የመግቢያ ህግ ነው።

እቺ መግቢያ ነች ስለተባለች ነው ‹‹ጀኖሳይድ ጀኖሳይድ ›› እየተባለ ያለው። የሚገርመው ነገር ጌታቸው ረዳ እራሱ በአፉ ጀኖሳይድ በሚል ቃል አልተናገረም። እሱ ‹‹ጀኖሳይድ ሊሆን የሚችል ነው›› ነው ያለው። የህግ ባለሙያም ስለሆነ ሙያውን መቀለድና ማበላሸት አልፈለገም። ተመልሰን የተናገረውን ካየነው ጀኖሳይድ እስኪደርስ ነው የሚለው፣ የዓለም ማህበረሰብ ምንም አያደርግም፤ ይህ የውስጥ አቅም ነው የሚወስነው፣ የውጭ የሚባል ነገር ምንም ትርጉም የለውም።

**አዲስ ዘመን፡- የትግራይ ህዝብ ሰላምና መረጋጋት እንዲያገኝ በምን መንገድ ነው አሸባሪው ሕወሓትን መቃወምና በቃህ ማለት የሚቻለው?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** መቃወም አይችልም። በአንድ አምባገነን (ዲክታተር) መንግስት ስር ሆኖ ህዝብ ምንም አቅም የለውም። ይህ እውነታው ያልገባው ነው እንዲህ የሚለው። የህዝብ መብት የሚከበረው በዲሞክራሲ ሀገር ነው። በዲሞክራሲ ሀገር ህዝብ መርጦ መንግስትን መጣል ይችላል፤ ከመንግስትነት ማላቀቅ ይችላል፤ ግን አምባገነን(በዲክታተር ) ስርዓት ውስጥ ያለው ህዝብ ግን ምን ሊያደርግ ይችላል? ያ ህዝብ ተጨቁኖ ነው ያለው። ይህ እየታወቀ የትግራይ ህዝብ እራሱ መነሳት አለበት የሚባል ነገር የለም።

እንዴት አድርጎ ነው የሚነሳው ማን እድል ይሰጠው? በጠመንጃ በጦርነት የተከበበ ክልል ፣ ልጆችህን ለጦርነት ካላዋጣህ ለትግል ካልሰጠህ ሀገርህ አይደለም በሚባልበት ሀገር እኮ ነው ያለው። እንደዚህ በሚባልበት ሁኔታ ህዝብ ተነስቶ ምን ሊያደርግ ነው? ህዝብ መነሳት አለበት መቃወም አለበት የሚለው ትርጉም የሌለው ነው። ለሃያ ሰባት ዓመት ወያኔ ህዝብ ሲያስተዳድር የትኛው ህዝብ ተነስቶ ያውቃል ? ለምን ታድያ አይገለብጠውም ነበር ? ህዝብ አንድ ላይ አይደል ሲገዛ የነበረው፣ አሁን ትግራይ ላይ ምን የተለየ ነገር አለ?

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ መንግስት ምን ቢያደርግ ነው የትግራይ ህዝብ ችግር ሲፈታ የሚችለው? ከመንግስት ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ሀገሩን የመከላከል ፣ ሀገሩን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት። የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ስልጣን ያለው ፌደራል መንግስት ነው። መከላከያ አለው፣ ሀይል አለው ሙሉ ስልጣን አለው። ለሽፈተ ሽፍታ፣ ህግ አላከብርም ለሚል ቡድን መንግስት ህግ የማስከበር ኃላፊነት አለበት። ከአንድ ሽፍታ ጋር እንዴት ነው ቁጭ ብሎ ውይይት የሚያደርገው። ከሽፍታ ጋር ቁጭ ብለህ ውይይት ማድረግ የሚያሳፍር ነው።

ህዝብና መንግስትን የሚያንቋሽሽ ሽፍታ እየተፈጠረ ዝም ብሎ የሚታይበት መንገድ እኔ አልቀበለውም። ስለዚህ መንግስት ኃላፊነቱ ይህ ነው ሌላ ነገር አይደለም። እነሱ ህግ ጥሰው ጠመንጃ አንስተው አይደል እየተዋጉ ያሉት ? መልሱ ይህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?**

**አቶ ኪዳነማርያም፡-** ይህ ጉዳይ በፖለቲካ ንግግር የሚያልቅ አይደለም። ይህ ጉዳይ ወታደራዊ ውሳኔዎች የሚያስፈልገው ጉዳይ እንጂ በንግግር የሚፈታ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ደክሞታል ፣ በዚህ ጉዳይ ሰልችቶታል። በሀገሩ ሰላም እያጣ ነው ያለው። በኢኮኖሚም እየተጎዳ ነው ያለው። በትግራይ ብቻ አይደለም በኢትዮጵያም የተረጋጋ ነገር የለም። እንዴት ተደርጎ ነው ወደ እድገት እና ልማት የሚኬደው? ይህ ነገር በሆነ መንገድ ማለቅ አለበት።

ይህ ህዝብ ሰላም ማግኘት አለበት። ደክሞታል። በጦርነት ምክንያት የትግራይ ህዝብ ብቻ አይደለም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው የሰለቸው። በግርግር የሚሆን ነገር፤ የሚመጣም ሰላም የለም። ሰላም ከማይፈልግ ፍጥረት እንዴት ነው ሰላም የሚመጣው? አሜሪካና አውሮፓ ሰላም ስላሉ የሚመጣ ሰላም የለም። እነሱ እዚህ ጋር ግድ የላቸውም። እነሱ በየትኛውም ዓለም ሰላም አድርጉ እያሉ ነው የሚናገሩት። እቺ ሰላም እንዴት አድርጋ ትምጣ? ነው ትልቁ ጥያቄ።

**አዲስ ዘመን፡-ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ኪዳነማርያም** ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የውጭ ባንኮች ለኢንቨስትመንት ፋይናንስ ተጨማሪ አቅም

አንተነህ ቸሬ

በአንድ አገር የልማት ጉዞ ውስጥ የማይተካ ሚና ካላቸው የምጣኔ ሀብት አንቀሳቃሾች መካከል የገንዘብ ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው። ከገንዘብ ተቋማት መካከል ደግሞ ባንኮች በግንባር ቀደምትነት ይመደባሉ። ባንኮች ለልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያና ለስራ እድል ፈጠራ የሚሆን ገንዘብ በቁጠባ አሰባስቦ በማቅረብ የአገራትን የልማት ጉዞ በመደገፍ ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

ኢትዮጵያ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን እውን ለማድረግ የያዘቻቸውን እቅዶች ለማሳካት እንዲያስችሏት በመንግሥትም ይሁን በግል ዘርፎች ለምታከናውናቸው የልማት ፕሮጀክቶች አስተማማኝ የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልጋታል። የዚህ የፋይናንስ ምንጭ ከሆኑ ገንዘብ አቅራቢ ድርጅቶች መካከል ባንኮች ዋነኞቹ ናቸው። ይሁን እንጂ የልማት ፕሮጀክቶችም ይሁኑ የግሉ ዘርፍ የሚፈልጉት ፋይናንስና የአገሪቱ ባንኮች አቅም የሚመጣጠን እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ሲገለጽ ቆይቷል።

ይህ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ደግሞ ለችግሩ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ በብዙ ወገኖች እንደ አንድ መፍትሄ የሚቀርበው የውጭ ባንኮችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት አሰራር በአማራጭነት እንዲነሳ ሲያደርግ ቆይቷል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስማቸው የሚጠቀሱ ትልልቅ የውጭ ባንኮች ወደ አገሪቱ ገብተው የብድር፣ የእርዳታ እንዲሁም ሌሎች የፋይናንስ ተግባራት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉበት አሰራር ሳይተገበር ቆይቷል። ከሳምንት በፊት ይፋ የሆነው የመንግሥት ውሳኔ ግን ለብዙ ዓመታት ዝግ ሆኖ የቆየው የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንደሚሆን አሳውቋል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 13ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የባንክ ዘርፍን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ለማድረግ በቀረበው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል። ምክር ቤቱ የባንክ ዘርፍ አገልግሎቶችን በእውቀትና በቴክኖሎጂ ለመደገፍ፤ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር፤ የፋይናንስ ዘርፉን ተወዳዳሪነት፣ ውጤታማነትና ቀልጣፋነት በመጨመር በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እንዲሳለጥ፤ የሥራ እድል ፈጠራውም እንዲጎለብት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነትንና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት ለማስመዝገብ የሚያስችል በተባለው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ውይይት አድርጎ ግብዓቶችን በማከል በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

መንግሥት የባንኩ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንደሚሆን አስቀድሞም በተደጋጋሚ ሲጠቁም ቆይቷል፤ የሀገር ውስጥ ባንኮችም ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸውን ዝግጅት እንዲያደርጉ መክሯል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰጡት ማብራሪያ፣ ስለፋይናንስ ዘርፉ አፈፃፀም ገለፃ አድርገው « … የመንግሥትና አብዛኞቹ የግል ባንኮች አዳዲስ ህንፃዎቻቸውን ሰርተው ጨርሰዋል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራም እየጀመሩ ይገኛል፤ ለውጥም አለ። ነገር ግን ባለፈውም እንዳነሳሁት አሁንም ደግሜ ማንሳት የምፈልገው ላለፉት 20 ዓመታት የኢትዮጵያ ባንኮች ሌላ ባንክ መጥቶ ሳይሻማቸው ብቻቸውን የሚሰሩበት እድል አግኝተዋል። በብዙ ምክንያቶች ይህንን ሁኔታ ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት አይቻልም።» ሲሉ አስገንዝበዋል። « ተጨማሪ ሀብትና ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ስለሚያስፈልገን ባንኮች እናመጣለን። ለምሳሌ፣ በጎረቤታችን ጅቡቲ፣ አንድ ሰው ዶላር ባንክ ውስጥ ለማስቀመጥ ለባንኩ መክፈል አለበት። ባንክ ዝም ብሎ ዶላር አይቀበልም። የግል ባንኮች በስፋት ባሉበት አገር የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት በንፅፅር ከእኛ ይሻላል። እኛ የውጭ ባንክ ሳናስገባ ዘግተን የቆየንበት ሁኔታ እስካሁን ላለው የጠቀመ ቢሆንም ከአሁን በኋላ ግን ባንኮች ራሳቸውን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በዘመናዊ አሰራር አዘጋጅተው ከፍ ላለ ውድድር መዘጋጀት ይኖርብናል» ሲሉ ገልጸዋል።

«ይህን እንደአንድ ማሳያ ለማመላከት፣ የዛሬ ስምንት ወር ገደማ የሞባይል ባንኪንግ ጀምረን ነበር። በስምንት ወራት ጊዜ ውስጥ 14 ሚሊየን ደንበኛ አፍርቷል፤ ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ተፈፅሞበታል። ይህ አብዛኛው ባንኮች ጋር የሚገኝ ቁጥር አይደለም። በስምንት ወራት ውስጥ ለዓመታት የሠሩ ባንኮችን አቅም መፍጠር የቻለው ቴክኖሎጂና ተደራሽነት እየሰፋ በሚሄድበት ሰዓት የባንኮች ሥራ ሊበለጥ እንደሚችል ያመላክታል» ብለዋል።

«እናም ባንኮች ዝግጅት አድርገው አሁን ያለውን እድገት ጠብቀው አገራዊ ባንኮች ይበልጥ በፉክክር ውስጥ አዳጊ መሆን እንዲችሉ ዝግጅት ያስፈልጋቸዋል። መንግሥት ከዚህ አንፃር የፖሊሲ ማሻሻያ ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ ነው። ቅድመ ሁኔታዎች ካለቁና ባንኮች ከተዘጋጁ ወደዚያ ሁኔታ ስለምንገባ የግል ባንኮችና የመንግሥት ባንኮች ከወዲሁ በተቀናጀና በተባበረ መንገድ ራሳቸውን ለውድድር ማዘጋጀት እንዳለባቸው ማሳሰብ ያስፈልጋል» በማለት አብራርተው ነበር።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ፤ ሀገር በቀል ባንኮች ከውጭ ባንኮች ጋር ለሚኖረው ውድድር ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ሲያሳስቡ መቆየታቸውም ይታወሳል። ዶክተር ይናገር ከባንኮች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በነበራቸው የውይይት መድረክ ላይ «ያልተደራጁ 20 እና 30 ባንኮች ከሚኖሩን ይልቅ ሁለት እና ሶስት ጠንካራ እና ተወዳዳሪ ባንኮች ቢኖሩን እንመርጣለን» ብለው ነበር። የውጭ ባንኮችም ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው መሥራት የሚያስችል የሕግ ማርቀቅ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ተናገረው ነበር።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ«ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)» ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መምጣት የተሻለ የኢንቨስትመንት ካፒታል ለማቅረብ እድል እንደሚፈጥር ይናገራሉ። ይህም ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፈንድ በማስገኘት በኢንቨስትመንት ዘርፉ ከውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለማቃለል እንደሚያግዝ ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ የባንኮቹ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ መሰማራት የሀገር ውስጥ ባንኮች በአቅም ውስንነት ምክንያት የተሻለ የኢንቨስትመንት ካፒታል ለመፍጠር ለሚቸገሩበት አሰራር እልባት ይሰጠዋል። መንግሥት የሀገር ውስጥ ባንኮችን ተወዳዳሪነት ለመጠበቅ ብሎ ገደብ ካላስቀመጠባቸው በስተቀር የውጭ ባንኮች የተሻለ ገንዘብ የማምጣት አቅም አላቸው። በተጨማሪም ባንኮቹ የየራሳቸው የአሰራር ስርዓት ቢኖራቸውም ዝቅተኛ የወለድ ምጣኔም (Lower Interest Rate) አላቸው። በአጠቃላይ ባንኮቹ በሀብትም ሆነ በወለድ ምጣኔ የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ይህም ተጨማሪና የተሻለ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ በማስገኘት የባንኮቹ ሚና ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት አወንታዊ ሚና እንዲኖረው ያደርጋል።

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ግጭቶች ባሉበት፣ የውጭ ጫናዎች በበረቱበትና ምጣኔ ሀብቱ ባልተረጋጋበት በዚህ ወቅት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንዲሆን መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚሉ ወገኖችም አሉ። ዶክተር ሞላ ግን በዚህ ሃሳብ አይስማሙም። «በመንግሥት በኩል የተላለፈው ውሳኔ ከአገሪቱ አለመረጋጋት ጋር የሚገናኝ አይደለም። መንግሥት የፖሊሲ ማሻሻያ ነው ያደረገው። ውሳኔው ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ አቅም በማስገኘት የተጎዳው የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲሻሻልና እድገት እንዲያስመዘግብ ያግዛል» ይላሉ።

በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ ግርማ በበኩላቸው፤ የባንኩ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንዲሆን የሚፈቅደው ረቂቅ ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል መወሰኑ የኢንቨስትመንት ካፒታል እንዲጨምር በማድረግ ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል። በሌላ በኩልም ለኢንቨስትመንት ማደግ ከሚኖረው አወንታዊ ሚና በተጨማሪ በጥንቃቄ ካልተመራ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስከትል እንደሚችል ረዳት ፕሮፌሰሩ ጠቁመው፣ ለእዚህም የኢንቨስትመንት ተወዳዳሪነት አቅምን ማሳደግ እንደሚገባ ይገልፃሉ።

«የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ሲሰማሩ ለአብዛኛው ሕዝብ የፋይናንስ አማራጮችን ይዘው እንደሚመጡ ይጠበቃል» የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ፣ የባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ መግባት በአገር ውስጥ ባንኮች የሚታየውን የብድር አቅርቦትና የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ በማቃለል የፋይናንስ አማራጮችን ለማቅረብ ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው ይገልፃሉ።

«የሐገር ውስጥ ባንኮች የኤሊቶች (Elites) መክበሪያ ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ ተገልጿል። ባንኮቹ በአብዛኛው ሃብታሙን የኅብረተሰብ ክፍል ያማከለ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። የፋይናንስ ተደራሽነት እውን የሆነው በጣም ጥቂት ለሆኑ አካላት ብቻ ነው። አብዛኛው ሕዝብ ከፋይናንስ ተደራሽነት የራቀ ነው።» ሲሉ አመልክተው፣ የባንኩ ዘርፍ እስካሁን ድረስም ለውጭ ኢንቨስተሮች ዝግ ሆኖ የቆየው የሀገር ውስጥ ባንኮችን ለመጠበቅ ታስቦ እንደሆነ ቢገለፅም ይህ ፉክክርን የመሸሽ ልማድ ግን ሊቀየር ይገባል» ይላሉ። «ፉክክርን መፍራት አያስፈልግም። የባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት አማራጭ የብድር አቅርቦቶችን ማግኘት የሚያስችሉ አሰራሮች ስለሚኖረው ውሳኔው ለድሃው ብቻ ሳይሆን መካከለኛ ገቢ ላለው የኅብረተሰብ ክፍልም መልካም ዜና ነው» ብለዋል።

የባንክ ዘርፍን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት የማድረግ እርምጃ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚፈልግ እንደሆነ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች መገንዘብ ይቻላል። ኢትዮጵያም የባንክ ዘርፏን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ስታደርግ በከፍተኛ ጥንቃቄ በታጀበ አሰራር ሊሆን እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ ይመክራሉ።

ዶክተር ሞላ መንግሥት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ለማድረግ ያሳለፈው ውሳኔ ትግበራው ጥንቃቄን የሚፈልግ እንደሆነ ያስረዳሉ። «የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የአገር ውስጥ ባንኮችን ካቀጨጩ በኋላ ጥለው የሚሄዱ ከሆነ ምጣኔ ሀብቱ ምስቅልቅል ውስጥ መግባቱ አይቀርም። መንግሥት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት የማድረጉን ሥራ በቅድመ ሁኔታና በሕጋዊ ማዕቀፎች በተደገፈ አሰራር እንዲተገበር ማድረግ አለበት» ሲሉ ያስገነዝባሉ። ባንኮቹ ለማን ብድር ማቅረብ እንዳለባቸው፣ አሠራራቸው የአገሪቱን ኢኮኖሚ ይበልጥ ሊጠቅም የሚችለው እንዴት ነው … የሚሉትን ጉዳዮች በጥልቀት በማጤንና ከባንኮቹ ጋር በመስማማት ወደ ሥራ መገባት ይኖርበታል ብለዋል።

ባንኮቹ ሥራቸውን መስራት ያለባቸው በአገሪቱ ሕግና ደንብ መሰረት መሆኑንም ጠቅሰው፣ ፖሊሲው የአገሪቱን ኢኮኖሚ በሚጠቅም መልኩ መተግበር እንዳለበት ይናገራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ እንዴት መሥራት እንዳለባቸው የሚያሳይ ግልጽ መመሪያና የአሠራር ስርዓት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ባንኮቹ ብድር ለማን እና እንዴት መስጠት እንዳለባቸው የሚያመለክቱ መመሪያዎች ሊያዘጋጁና ክትትሎችም ሊደረጉ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም የፋይናንስ አካታችነት (Financial Inclusiveness) እንዲኖር ማድረግም ተገቢ ነው። የተሻለ የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅም ላላቸው እንዲሁም ከአገር ውስጥ ባንኮች ጋር በቅንጅት መሥራት የሚፈልጉ ካሉ ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባም ይመክራሉ።

የባንክ ዘርፉ ለውጭ ኢንቨስትሮች ክፍት ሲደረግ አሳሳቢ ከሚሆኑት ጉዳዮች መካከል የአገር ውስጥ ባንኮች ተወዳዳሪነትና ህልውና አንዱ ነው። የውጭ ባንኮች ካላቸው የገንዘብና የቴክኖሎጂ አቅም አንፃር የአገር ውስጥ ባንኮች በገበያው ላይ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ይቸገራሉ የሚለው ጉዳይ የብዙ ወገኖች ስጋት ነው። በዚህ ረገድ ዶክተር ሞላ «የውጭ ባንኮች በሀብት፣ በእውቀትና በቴክኖሎጂ የዳበሩ በመሆናቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ዓለም አቀፍ የባንክ አሰራር ልምድ የሌላቸውን የሀገር ውስጥ ባንኮችን ጫና ውስጥ ይከቷቸዋል። ባንኮቹ አሁን ባላቸው ቁመና ከውጭ ባንኮች ጋር ሊወዳደሩ አይችሉም። መንግሥት የአገር ውስጥ ባንኮች አንድ ላይ ተጣምረው በመስራት ጠንካራ እንዲሆኑ ደጋግሞ መክሯል። ስለሆነም የሀገር ውስጥ ባንኮች ተጣምረው ከመስራት በተጨማሪ ከውጭ ባንኮች ጋር በቅንጅት መሥራት ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎችም ማሰብ ይኖርባቸዋል» ሲሉ ይጠቁማሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ ደግሞ «ባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ በሌሎች አገራት ውስጥ ያላቸውን የአሠራር ስርዓት ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ይዘው ይመጣሉ ማለት አይደለም። ለባንኮቹ የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ አሰራሮች ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል። መንግሥት፣ ባንኮቹ የሚንቀሳቀሱባቸውን መመሪያዎች በማዘጋጀት የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር አለበት» በማለት የባንኩ ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት የማድረግ እርምጃ ትግበራው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ እንደሆነ ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ አገራት ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የሚተገበር የአሠራር ሥርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን ቀደም ሲል አስታውቆ ነበር። ባንኩ የሚያዘጋጀው የአሠራር ስርዓት የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ መግባት ከሚያስገኘው ጠቀሜታ ባሻገር በሂደቱ ሊያስከትል የሚችለውን ስጋት ሊቀንስ የሚችል የሕግ ማዕቀፍን ያካተተ እንደሆነ በብሔራዊ ባንክ የባንክ ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ፍሬዘር አያሌው መናገራቸው ይታወሳል።

**የውጭ ባንኮች በሀብት፣ በእውቀትና በቴክኖሎጂ የዳበሩ በመሆናቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ዓለም አቀፍ የባንክ አሠራር ልምድ የሌላቸውን የአገር ውስጥ ባንኮችን ጫና ውስጥ ይከቷቸዋል። ባንኮቹ አሁን ባላቸው ቁመና ከውጭ ባንኮች ጋር ሊወዳደሩ አይችሉም። መንግሥት የአገር ውስጥ ባንኮች አንድ ላይ ተጣምረው በመስራት ጠንካራ እንዲሆኑ ደጋግሞ መክሯል። ስለሆነም የአገር ውስጥ ባንኮች ተጣምረው ከመስራት በተጨማሪ ከውጭ ባንኮች ጋር በቅንጅት መሥራት ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎችም ማሰብ ይኖርባቸዋል**

# ጎሜ

# ሃሰተኛ በቃሉ ...

**ምሕረት ሞገስ**

የግሮሰሪው አስተናጋጅ ደስ ብሎታል። በዓል መሆኑ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ብቻ እየተፍነከነከ ያስተናግዳል። ለካ ገብረየስ ገብረአምላክ እንደድሮው ሽጎጥ ሳያደርግለት አልቀረም። አስተናጋጁ ፈንጠዝያ ላይ ነው። የበዓል ማግስት በመሆኑ የአዲስ ዘመን ድባብ ገና አልደበዘዘም። በደስታ ሥራውን እያሟሟቀ ያለው አስተናጋጅ ዓመቱ ምርጥ ሆኖ እንደሚያልፍ ከወዲሁ የታየው ይመስላል።

ገብረየስም የአስተናጋጁ ደስታ ተጋብቶበታል። እርሱም ዘመኑን ሰፋ አድርጎ ተደስቷል። ዘውዴ መታፈሪያ ወደ ግሮሰሪው ሲገባ ገብረየስ በፈገግታ ተቀበለው። ዘውዴም ከገብረየስ በላይ ፈገግ አለ። ዘውዴ ለገብረየስ ‹‹ከፎከረ ይሻላል የጠረጠረ የሚባለው የገባህ በህይወትህም ተግብረኸው ውጤት ያገኘኸበት አንተ ነህ። አንዳንዶች ቸኩለው ስህተት ላይ ሲወድቁ አንተ ግን የወያኔን ነገር ተከታትለህ እና መርምረህ ውሸታምነቱን አውቀህ እውነት ላይ መድረስህ አትርፎሃል። ሌሎቹ ግን የሃሰተኛው ወያኔ ዋነኛ ዘዴው በማስመሰል የሚፈልገውን ማግኘት መሆኑን ረስተው እና በውሸት ህዝቡንና ራሱን በማታለል የሚታወቀውን ወያኔን አምነው ጉድ ሆኑ።

ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ሆኖባቸው ከጥፋተኛ ጋር አብረው ያልታሰበ ነገር ገጠማቸው፤ ያልታሰበ ዱብዳ ወረደባቸው። ላስተዋለ የወያኔ ነገር ሁልጊዜም የህልም ሩጫ እና የማይጨበጥ ነው። እርሱን ማመን ፈፅሞ አይታሰብም፤ ሌላው ቢቀር በየአጋጣሚው የሚሰጠውን መግለጫ በማየት አንዴ ጥቁር ሌላ ጊዜ ደግሞ ነጭ ነኝ ማለቱን ብቻ ተመልክቶ ከእርሱ ጎን መሆንን ማቆም ይገባ ነበር።አሁን አሁንማ መገለጫ ባህሪዎቹ ቁልጭ ብለው ወጥተዋል። ›› አለ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹በዚህ ዓመት ሁሉም ነገር ያበቃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በአዲስ አመት የመጀመሪያ ቀን ‘ካለ ቅድመ ሁኔታ እንደራደራለን’ ብለዋል። ምናልባት ውሸታቸውን እንደሚሆን አስባለሁ። ምክንያቱም የእነርሱ ነገር ሁልጊዜም ከሰው የተለየ ነው። ተፈጥራዊ ባህሪያቸውም ማጭበርበር፣ ማታለል መዋሸትም አይደል። አሁንም ዓለማቀፉን ማህበረሰብ ለማታለል ያደረጉት ይመስለኛል። መንግስት እንኳን አይታለልላቸውም ጠንቅቆ ያውቃቸዋላ ያው እንደለመዱት የጸጥታው ምክር ቤት ስብሰባ ከማካሄዱ በፊት ለማደናገሪያ ይመስለኛል። የእኛ ሰው አፍ ቢዋሽ ሆድ ይታዘባል ይላል። ውሸት ለህሊና ደስ ካለማለቱ በተጨማሪ የተዋሸ ነገር በኋላ ራስን በራስ እስከመታዘብ ያደርሳል። የአሸባሪው ቡድን አባላት ግን ራሳቸውንም ለመታዘብ የሚበቁ አይደሉም፤ ታሪካቸው የሚያሳየው ቃል እየገቡ ቃልን ማጠፍ ነው።ቃላባይ እንደሚባሉት አይነት ናቸው። ነገር ግን እነርሱ እንኳን ራሳቸውን ባይታዘቡ ሌላው ከጎናቸው የቆመ ለመታዘብ ጊዜ ባልፈጀበት ነበር፤›› ሲል፤ ተሰማ መንግስቴ ከደጅ ገብቶ ተቀላቀላቸው።

ዘውዴ ተሰማን ሰላም ካለ በኋላ ‹‹በሚገርምህ መልኩ ወያኔ በቅርቡ ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ በምን ቀን ምን እንዳለ ፅፌ ነበር። አሁን የደረሰበትን ስሰማ፤ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ቃል እየገባ እንዴት እንደሚዋሽ ስመለከት አስገርሞኛል።›› አለ። ተሰማ በበኩሉ በምን ቀን ምን አለ? ብሎ ዘውዴን ሲጠይቀው ‹‹አይ! ይህንን እንደውም ከኔ በላይ መከታተል የነበረብህ ራስህ ነበርክ።›› ሲል ምላሽ ሰጠ። ተሰማ በዘውዴ መልስ አልተከፋም። ‹‹የእኔ ዘርፍ ይህንን የሚመለከት አይደለም። ዜናውን እሰማለሁ ነገር ግን ቀኑን መዝግቦ ማስቀመጥ የኔ ድርሻ አይደለም።›› ሲል ተሰማ በበኩሉ ለዘውዴ ምላሽ ሰጠ።ምን መመዝገብ ያስፈልጋል ማስታወሱ በቂ ነው።

> **አሁን ሕወሓት ለትግራይ ህዝብ ብዙ ነገር ዘላብዷል። በሰዎች ዘንድ በደንብ ሲያስገምተው ወይም ቅሬታ ሲያስከትል የሚችል እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦችን ሲያስተሳልፍ ዓመታትን አስቆጥሯል።ህዝቡን ሲያሳስትና ሲያደናብር ከርሟል፤ አያስተውልምና ይህ ሳያሳፍረው ይችላል**

ዘውዴ፤ ‹‹እንኳን ፖለቲከኛ እና ባለስልጣን እኔም ዜናውን ሰማቼ እንደተራ ነገር አላልፈውም። እያንዳንዱ መግለጫ ምክንያት እና ትርጉም አለው። ተሴ እንደ ደረጃህ አተኩር፤ ፖለቲካ ብሎ ቀልድ የለም። ገብረየስ ነቅቶ ከወያኔ ተለይቶ ራሱን ችሎ በመቆሙ ከጥፋት ራሱን እና ቤተሰቡን ታድጓል። ፖለቲካ እና ስልጣን ላይ መሸወድ መታለል አያስፈልግም። እንዲሁ በደምሳሳው ሳይሆን ትኩረት ሰጥቶ እያንዳንዱን ነገር መከታተል ያስፈልጋል።ላለመርሳት መፃፍ ምርጥ አማራጭ ነው›› ሲል ገብረየስ እና ተሰማ ሁለቱም ተያዩ ዘውዴ ትክክል መሆኑን እንዳመኑ ጭንቅላታቸውን ነቅንቀው በምልክት ገለፁ።

ተሰማ ከዘውዴ ቀጠለና ‹‹ እርሱማ ትክክል ነህ። ፖለቲካ እና ስልጣን በስንፍና እና ሰዎችን በማመን የሚሆን አይደለም። እውነት ነው ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነውና ሥራን መሥራት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄ መከታተል ይገባል። እውነት ለመናገር ምንም እንኳን ሥራዬ ላይ ብተጋም እስከ መፃፍ የደረሰ ክትትል አድርጌ አላውቅም። ግን እንደው እውነት የፃፍከውን ንገረኝ እና በእነርሱም በአንተም ልገረም›› ሲል ጠየቀው።

ዘውዴ በበኩሉ ‹‹ቲፒኤልኤፍ ሐምሌ 25 በምንም ተአምር በአፍሪካ ህብረት አንደራደርም ሲሉ መግለጫ ሰጥተው ነበር። ሐምሌ 26 ተወረናል፤ የሰላም በር ተዘግቷል፤ እናም ወረራውን ለመቀልበስ ማንኛውንም እርምጃ እንወስዳለን ሲሉ ተሰምተዋል። ሰላማችንን በክንዳችን እያለም ፎከሯል። በአንድ በኩል ለህዝቡ ጀግኖች ነን በማንም አንደፈርም፤ እያሸነፍን እየገሰገስን ነው እናንተ ብቻ እርዱን ልጆች አምጡ አዋጡ እያለ ያቅራራል፤ በሌላ በኩል ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያለቃቅሳል። የድረሱልን ጥሪው ሁሌም በመሬት ያለው አልሆን ሲለው የሚያሰማውም አይደል። ››ብሎ ቀጠለ ማስታወሻውን ገልበጥ ገልበጥ እያደረገ። ‹‹ጦርነቱ እስከ አሁን 100 በመቶ የጦር መሳሪያዎቻችንን ያሳተፈ ሲሆን፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ገድለን በሺዎች ደግሞ ማርከናል›› ሲሉ ሐምሌ 28 ላይም ለፍፈው ነበር። ነሐሴ 26 መላው ‹የትግራይ ሃይል ወረራውን ይቀለብሳል› የሚል መግለጫ ሰጡ። መሬት ላይ ባለው ሽንፈት ምክንያት ደግሞ ሌላ ተቃራኒ ዘፈን ማሰማት ጀመሩ። የፀጥታው ምክር ቤት በኃይል ጣልቃ መግባት አለበት ሲሉ። ነሐሴ 30 አሜሪካ የትግራይን ሃይል መርዳት አለባት ካለ በኋላ፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአፍሪካ ሕብረት እንደራደራለን ሲሉ መግለጫ ሰጡ። በአፍሪካ ሕብረት አንደራደርም ካሉ ገና ሁለት ወራቸው ነው። ወዲያው ሽንፈትን ሲከናነቡ ደግሞ ያለቅድመ ሁኔታ እንደራደራለን አሉ።›› ሲል የፃፈውን ነገራቸው።

ገብረየስ ‹‹ መሸነፋቸው እና የትግራይ ሕዝብ ነፃ ለመውጣት ጫፍ ላይ መድረሱን ተረድቻለሁ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ፍፁም የሚታመኑ አይደሉም። በእርግጥ አሁን ከአፍ የወደቀ ጥሬን ያህል ትንሽ እንኳን አቅምና ተስፋ አላቸው ብዬ አልገምትም። ነገር ግን ደግሞ ያበቃላቸው ቢሆንም ተስፋ አይቆርጡም የትግራይን ህዝብ ማስፈጀታቸውን እስከሚሞቱም ድረስ ቢሆን ያቆማሉ ብዬ አልገምትም ›› አለ።

ተሰማ ደግሞ ‹‹ጥጋብ ሲበዛ በራስ ላይ ችግር ያስከትላል፤ ማለት ማሳያው ወያኔ ነው። የሽብር አባላቱ ጠግበው ነበር። ባይጠግቡ ኖሮ ሕዝብ ለመጨረስ እና ለማስጨረስ አያስቡም ነበር። በዓለም የሽብር ቡድን የሰው ልጆችን በማስፈጀት ታሪክ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ብዬ እገምታለሁ። ምናልባትም ካለፈው የውሸት ታሪካቸው እንደምንረዳው የሚያስፈጁት ህዝብ እስከሚያልቅ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረጋቸው አይቀርም። እንደራደራለን ይበሉ እንጂ በትክክል ይደራደራሉ የሚል እምነት የለኝም።ምክንያቱም እነሱ ካለ ጦርነት መኖር አይችሉም። ካለጦርነት መዝረፍ አይችሉም። ስለዚህ ሰላምን አይፈልጉም›› አለ። ልክ ነው በሚል ምልክት ሁሉም ራሳቸውን ነቀነቁ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹እኔ ደግሞ በተለይ የሰሞኑን ድርጊታቸው ከአፈርኩ አይመልሰኝ አንዴ ከተናገርኩ ስህተቴን አላርምም በማለት የድርቅና አካሔድ ይመስለኛል። ምንም ዓቅም ሳይኖራቸው መንገታገት እንኳን ድል ራስን የማዳኛ ዕድልንም ያጠፋል።›› ሲል ዘውዴ ቀበል አድርጎ ‹‹እንግዲህ ከአፍ የወጣ ነገር አመጣ ነው። ከአፍ ያመለጠ መጥፎ ነገር ያልታሰበ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል እንደፖለቲከኛ ማወቅ ነበረባቸው። ነገር ግን ተሰማ እንዳለው ጠገቡ፤ ‹ ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ› ሆነባቸው እና በደንብ ዘለሉ፤ የሚሰበሩ አልመሰላቸውም ነበር። ነገር ግን የሚሰበሩበት ጊዜ ደረሰ። ›› አለ። በእዝነ ልቡናው መለስ ብሎ የስልጣን ጊዜያቸውን እያስታወሰ፤ አኳኋናቸውን እያሰበ ለራሱ ተገረመ።

ዘውዴ በበኩሉ ገብረየስን እያየ፤ ‹‹ ከአፍ ወለምታ የእግር ወለምታ ይሻላል፤ ታሽቶ መዳን ይቻላል። ወደ ነበሩበት መመለስ ቀላል ነው። አፍ ሲያመልጥ ግን በቀላሉ ወደ ነበረበት መመለስ አይቻልም። ለአዋቂ እና ለአስተዋይ በስህተት መናገር በኋላ መዘዙ ብዙ ነውና ያሳፍራል፤ አሁን ህወሀት ለትግራይ ህዝብ ብዙ ነገር ዘላብዷል። በሰዎች ዘንድ በደንብ ሊያስገምተው ወይም ቅሬታ ሊያስከትል የሚችል እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦችን ሲያስተላልፍ ዓመታትን አስቆጥሯል።ህዝቡን ሲያሳስትና ሲያደናብር ከርሟል፤ አያስተውልምና ይህ ላያሳፍረው ይችላል። ነገር ግን አሁን የሽብር አባላቱ ከአፍ የወጣ ቃል ከእጅ ያመለጠ እንቁላል ነውና አሁን ያለፈውን ዕድል የሚያገኙበት ጊዜ አምልጧል። ከአሁን በኋላ መመለሻ የለውም፤ ነገር ግን ቢያንስ አሁን የትግራይ ህዝብ ራሳቸውን መመለስ እና ቀልባቸውን ሰብስበው ከውሸታሞቹ ጋር መተባበርም ሆነ አብሮ መቆምን ካላቆሙ ያልታሰበ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ማወቅ አለባቸው።

የሰው ልጅ መሻት እና ፍላጎት ትልቅ መሆኑ የሚካድ አይደለም። ምንም ነገር ቢያገኝ ባለው ላይ ተጨማሪ ነገር ማሰቡ አይቀርም። ነገር ግን ያንን ለማግኘት የሰውን ህይወት ማወራረጃ ማድረግ በጣም አስፈሪ እና አሳፋሪ ነው። የሽብር ቡድኑ አባላት ቢያንስ የያዙትን ይዘው መቆየት ይችሉ ነበር። ለትግራይ ሕዝብም የሚያስቡ ቢሆን ከአንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም እና ተጎድተውም ቢሆን የትግራይ ህዝብ ይህንን መሳይ ችግር በድጋሚ እንዳያጋጥመው ማስተዋል ይጠበቅባቸው ነበር። ነገር ግን የለመደ ልማድ ያስቀራል ከመዓድ ነውና የተጠናወታቸው የጦርነት እና ሰው የማስፈጀት ልማድ በቀላሉ የማይለቅ በመሆኑ ህዝቡን ጎዱ፤ አሁን ደግሞ ቅጥፈታቸው ውርደት ላይ እየጣላቸው ነው።›› ሲል ዘውዴ ረዥም ንግግሩን ቋጨ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹ እውነት ነው፤ በእርግጥ ለትግራይ ሕዝብ የቆሙ ከሆነ ሕዝብን እያታለሉ የትውልዱን ደም ከሚያፈሱ የትግራይን ሕዝብ ከዚህ መሳይ ችግር የሚያወጣውን መንገድ ማመቻቸት አለባቸው። አስፈላጊ ከሆነ እውነት እነርሱ ትንሽም ብትሆን የሰውነት ስብዕና ካላቸው ቢያንስ ዛሬ ራሳቸውን ሰውተው የትግራይን ሕዝብ ካለበት ስቃይ መገላገል አለባቸው። ሕዝቡን ለመርዳት ከታሰበ የሚፈለገውን ነገር ለመስጠት መንገድ አይጠፋም። ዛሬ በዚህ ዓመት ይህን ያደርጋሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በታሪክ የታወቁ ፤ዓለም የመሰከረላቸው ውሸታሞች ቢሆኑም ቢያንስ ዛሬ ጦርነቱን በማቆም ወደ ድርድር ቢገቡ በእውነት በጣም ደስተኛ እንሆን ነበር።›› ብሎ እንባ ያረገዘ አይኑን አሸት አደረገ።

ተሰማ ገብረየስን አቀፍ አድርጎ ፤ ‹‹አይዞህ ወንድሜ ሃሰተኛ በቃሉ ስደተኛ በቅሉ በማለት ወያኔ እደራደራለሁ ማለቱን ለማመን ቢያዳግተንም በያዝነው ዓመት ትግራይ ከወያኔ ነፃ ትወጣለች፤ ሰላምም ይሆናል ፤በዚህ ላይ ጥርጣሬ አይግባህ ።›› ብሎ ለማባበል ሞከረ።

ገብረየስ የመጀመሪያ ፈገግታው ተመለሰ። በወያኔ ምክንያት ለዘመናት ብዙ ዋጋ የከፈለ በመሆኑ ተሰማ ‹‹ትግራይ ከወያኔ ነፃ ትወጣለች›› በማለቱ ዛሬ የተለየ ስሜት ተሰማው። በተስፋ ተሞልቷልና የራሱን ብቻ ሳይሆን ዘውዴ እና ተሰማ የጠጡበትን የሁሉንም ሒሳብ ከፍሎ ከግሮሰሪው ሲወጣ ቢያቀረቅርም ረዥምነቱ ጎልቶ ታየ። ዘውዴ እና ተሰማ ግን ትንሽ መቆየት በመፈለጋቸው እየተወያዩ ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ መጠጣታቸውን ቀጠሉ።

# የዘመን አቆጣጠራችን ጥበብ

ዋስልኝ አየለ

እነሆ አዲስ ዓመትን ከተቀበልን ዛሬ 5ኛ ቀናችን ሆነ። ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ጥበብ ያላት አገር መሆኗ አንዱ ቅኝ ያለመገዛቷ መለያ ነው።ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠርን የቀመሩ ሊቃውንት ያላት አገር ናት።

በአዲስ ዓመት ማግስት ላይ ሆነን እስኪ ሊቃውንት ያስቀመጡልንን የዘመን አቆጣጠራችንን ጥበብ እንቃኝ። በነገራችን ላይ እንቁጣጣሽን ከሌሎች በዓላት ለየት የሚያደርገው በዕለቱ ብቻ አይደለም የሚከበረው። ከዕለቱ ቀደም ብሎ ባሉ ቀናት በልጃገረዶች ጨዋታ እና ከበዓሉም በኋላ በአዲስ ዓመት አዳዲስ ሥራዎችና የትምህርት ቤቶች መከፈት ነው። ምክንያቱም የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነው።

እንቁጣጣሽ፤ ባህል ነው፣ ሃይማኖት ነው፣ ጥበብ ነው፣ ሳይንስ ነው። ባህል ነው ስንል የልጅ አገረዶችን ጨዋታ ጨምሮ ብዙ ባህላዊ ክዋኔዎቹ ማሳያ ይሆኑናል። ሃይማኖት ነው ስንል በተለይም በኦርቶዶክስ አማኞች ዘንድ ሃይማኖታዊ አከባበር ስላለው ነው። ጥበብ ነው ስንል ከግጥምና ዜማ ጀምሮ ብዙ ጥበባዊ ትውፊቶች ስላሉት ነው። ሳይንስ ነው ስንል የዘመን አቆጣጠራችን መነሻ ስለሆነና ሳይንሳዊ ቀመሮች ስላሉት ነው። በሳይንሳዊ ባህሪው ከፊዚክስና ሒሳብ ያልተናነሱ ቀመሮችንም በዚሁ ጽሑፍ እናያለን።

እንቁጣጣሽ ከሌሎች በዓላት ሁሉ ይለያል። ሌሎች በዓላት ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ይዘታቸው ይጎላል። ለምሳሌ መስቀል፣ ገና፣ ፋሲካ ብንል ሃይማኖታዊ ይዘታቸው ይበልጣል። ጥምቀት፣ አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል ብንል መነሻቸው ሃይማኖታዊ ይሁን እንጂ ባህላዊ ይዘታቸው ጎልቶ ይታያል።

በሌላ በኩል እንቁጣጣሽ የእነዚህ ሁሉ በዓላት ማስጀመሪያ ነው። ለምሳሌ የ2015 ዓ.ም መስቀል፣ የ2015 ዓ.ም ገና፣ ጥምቀት፣ አረፋ፣ መውሊድ፣ ፋሲካ፣ አሸንዳ... እያልን የምንጠራው እንቁጣጣሽ በቀየረው ዓመት ነው። እንቁጣጣሽ ብዙ ጥበብና ሳይንስ የያዘ በዓል ነው። ይህ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ባህሪው ሃይማኖት ዘለል በዓል ያደርገዋል።

በብዙ ነገሮቻችን ሁሉ «የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን» እያልን እንጠራለን። ኢትዮጵያ ልዩ የሚያደርጋትም ይሄው ነው። «የ13 ወር ፀጋ» በሚል ትታወቃለች። ይሄ ደግሞ ከዓለም ለየት ያደርጋታል። ይሄ ሁሉ የሆነው በዘመን አቆጣጠራችን ጥበብ እና ሳይንስ ነው። የዘመን አቆጣጠራችን ኢትዮጵያ ምን ያህል የመጠቁ ሊቃውንት እንደነበሯት ያሳያል። የእንቁጣጣሽ ጥበባዊና ሳይንሳዊ ቀመር ምስክራችን ነው። ብዙዎቻችን ልብ የማንላቸው (አንዳንዴም ሃይማኖታዊ እየመሰለን) ሳይንሳዊ ቀመሮች አሉት። ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከልዩ ልዩ ሰነዶች መረጃዎችን በማሰባሰብ ስለዘመን አቆጣጠራችን እናስነብባችሁ።

የስነ ጽሑፍና የስነ ከዋክብት ተመራማሪው መምህር አብነት ስሜ በ2008 ዓ.ም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ ጽፈዋል።

«የሀገራችን የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚጠቀሙበት የጊዜ ስሌት እንደሚከተለው ነው።

1 ዕለት = 60 ኬክሮስ

1 ኬክሮስ = 60 ካልዒት

1 ካልዒት = 60 ሣልሲት

1 ሣልሲት = 60 ራብዒት

1 ራብዒት = 60 ኀምሲት

1 ኀምሲት = 60 ሳድሲት

በዚህ መሠረት አንድ ዓመት 365 ዕለት እና 15 ኬክሮስ ይባላል። 15 ኬክሮስ ሩብ ዕለት ወይም 6 ሰዓት ነው። በሌላ አገላለፅ 1 ኬክሮስ 24 ሰዓት ስለሆነ 15 ኬክሮስ 360 ደቂቃ ነው። 360 ደቂቃ ደግሞ 6 ሰዓት ነው።

365 ዕለት፣ 5 ሰዓት፣ 48 ደቂቃ እና 46 ሰከንድ የተባለው አንድ ዓመት በባሕረ ሐሳብ የጊዜ ክፍፍል 365 ዕለት፣ 14 ኬክሮስ፣ 30 ካልዒት፣ 11 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ይሆናል። የ11 ደቂቃ እና 14 ሰከንድ ጉድለት የተባለው በባሕረ ሐሳብ ቀመራ መሠረት ጉድለቱ 29 ካልዒት፣ 48 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ነው የሚሆነው። 5 ሰዓት፣ 48 ደቂቃ እና 46 ሰከንድ ሲጠጋጋ 6 ሰዓት እንደሚሆነው ሁሉ 14 ኬክሮስ፣ 30 ካልዒት፣ 11 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ወደ 15 ኬክሮስ ይጠጋጋል።

የዓመቱ ዕለት እና ዝርዝሩ ከላይ እንደተቀመጠው ነው፤ ለልዩ ንጽጽር የተፈለገ ለየት ያለ ቀመር ግን ይታያል። ይኸ ቀመር አንድን ዓመት 365 ዕለት፣ 15 ኬክሮስ እና 6 ካልዒት ያደርገዋል።

በዚህ አካሔድ 15 ኬክሮስ ራሱ ተጠጋግቶ የተገኘ ሆኖ ሳለ እንደገና 6 ካልዒት ተጨምሯል። 6 ካልዒት 2 ደቂቃ እና 24 ሰከንድ ነው። ይህ በየዓመቱ በትርፍ የሚገኘው 6 ካልዒት በ600 ዓመት ውስጥ ተጠራቅሞ አንድ ዕለት ይሆናል። 6 x 600= 3600 ካልዒት= 60 ኬክሮስ= አንድ ዕለት። 2 ደቂቃ እና 24 ሰከንድም በ600 ሲበዛ 24 ሰዓት ወይም አንድ ዕለት ይሰጠናል።

እንግዲህ በየዓመቱ በተጠጋጋ ትረፍ የሆነው 6 ሰዓት በ 4ዓመት ተጠራቅሞ 24 ሰዓት ወይም አንድ ዕለት አስግቶኝ ጳጉሜን በ4 ዓመት አንዴ 6 እንደሚያደርጋት ሁሉ የ6 ካልዒት ትርፍ በ600 ዓመት አንዴ ጳጉሜ 7 ትሆናለች»

ቀመራዊ አሰራሩ እንዲህ በቀላሉ የሚገባን አይመስለኝም። ከዚህ የምንረዳው አባቶች ምን ያህል ሊቅ እንደነበሩ ነው። እነዚህን ሽርፍራፊ ቁጥሮች ደማምረው ነው ጳጉሜን የፈጠሯት። ጳጉሜንም አምስት፣ ስድስት እና ሰባት ያደረጓት። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከፈረንጅ ምንም ነገር ሳይኮርጁ እንደሰሩት ማረጋገጫ ይሆናል። በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ጳጉሜን የሚባል ወር የለም። ግን ያሏቸው 12 ወራት በየወሩ ቋሚ (30 ቀናት) አይደሉም። የእነርሱ ወር ከ28 እስከ 31 ባሉት ውስጥ ይዋዥቃል። የኢትዮጵያ ወራት ግን ሁሉም 30 ቀናት ናቸው። 13ኛዋ ወር ጳጉሜን ከላይ በቀረበው ስሌት መሰረት ሰርተዋታል።

እንቁጣጣሽ እንዲህ አይነት ሳይንሳዊ ቀመር ቢኖረውም ሃይማኖታዊ ይዘትም አለው። ለአራት የተካፈለበት ምክንያትም በአራቱ ወንጌላውያን (ማቲዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ) ነው። ጥቅል መጠሪያው (በብዙዎች የሚጠራው) እንቁጣጣሽ በሚለው ቢሆንም ሌሎች መጠሪያዎችም አሉት። እነዚህ መጠሪያዎች ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ናቸው። እንቁጣጣሽ ከሚለው ጀምረን እንያቸው።

ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ የጠቢቡ ሶሎሞንን ዝና ሰምታ ኢየሩሳሌም ተጉዛ ስትመለስ «እንቁ ለጣትሽ» በማለት ከእንቁ የተሠራ የጣት ቀለበት ንጉሥ ሰሎሞን እጅ መንሻ እንዲሆናት አበረከተላት። ይህን ታሪክ መነሻ አድርገው «እንቁጣጣሽ» የሚለው ስያሜ ከዚያ እንደመጣ የታሪክ ድርሳናት ያስረዱናል። በኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ዕለት ምድሪቱ በክረምቱ ዝናብ ውሃ እና ጭቃ ሆና የቆየችው ጭቃና ጎርፉ ተወግዶ በአረንጓዴ እጽዋት ተውባ ሜዳው፣ ሸለቆውና ተራራው በአደይ አበባ ተንቆጥቁጠው የሚታዩበት ወቅት በመሆኑ ዕለቱ «እንቁጣጣሽ» እንደተባለም ይነገራል።

ሌላኛው መጠሪያው «ዘመን መለወጫ» የሚለው ነው። ይሄ ደግሞ ሳይንሳዊ ምክንያትን የሚከተል ይመስላል። ዘመን መለወጫ መስከረም ወር የሆነበት ምክንያት ብርሃንና ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜን ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው የሚሉም አሉ። ሌሊቱ ከቀኑ ጋር ይስተካከላል። የዓመቱ ቀናት 364 እና 365 (የጳጉሜን 5 እና 6 መሆን ተከትሎ) እየተባሉ የሚጠሩም በዚህ አቆጣጠር ነው። በሃይማኖታዊ ምክንያት ደግሞ በኖህ ዘመን ተጥለቅልቆ የነበረው የጥፋት ውሃ የጎደለበት ወር ስለሆነ መስከረም የዘመን መለወጫ እንደተደረገ የሃይማኖት አባቶች ይናገራሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ የሚል መጠሪያም አለው። ይሄኛው መጠሪያ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ የተባለውም የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል መነሻ በመሆኑ ነው።

በዚህም ምክንያት በድርሳነ ዮሐንስ (ከገጽ 1 እስከ 3) እንደተገለጸው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መስከረም አንድ ቀን እንዲከበር አባቶች ወስነዋል። መጽሐፈ ስንክሳር «የመስከረም ወር የተባረከ ነው፣፤ እርሱም የግብጽና የኢትዮጵያ ዓመቶች መጀመሪያ ነው። የዚህ ወር ቀኑና ሌሊቱ እኩል 12 ሰዓት ነው። ከዚህ በኋላ ቀኑ እየጎደለ ይሄዳል» ይላል።

ስለዘመን ቀያሪው እንቁጣጣሽ ስሞችና ቀመሮች ይህን ካልን የዘመን አቆጣጠራችን ከሌሎች የዓለም አገራት ለምን እንደተለየ ደግሞ ሊቃውንት የሚነግሩንን እንመልከት።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ «ባሕረ ሐሳብ» በሚል መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከምዕራባውያን የተለየበትን ምክንያት ሲገልጹ «ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገው ይጠቀማሉ፤ ታላቁ እስክንድርም የገነነበት ዘመን መቁጠሪያቸው ሆኖ ነበር» ይላሉ። የኢትዮጵያ ካህናትም ዘመነ እስክንድር በሚል ይጠቀሙበት እንደነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ሶርያውያን የዘመን አቆጣጠራቸውን የሚለኩት በፀሐይ ቆጥረው የዓመቱን 365 ቀን ለስድስት አካፍለው ከሮማውያን በተዋሱት ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ አዲስ ዓመት ይሉታል። በኋላ የሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓመተ ዓለም ወደ መስከረም 1 ቀን ለወጡት። የአገራችን ሊቃውንትም አዲስ ዓመታችን መስከረም አንድ ቀን እንዲሆን የወሰኑት ይኸንን በመከተል ነው። የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብጾች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ይገዛ የነበረው ዩልዮስ ቄሣር ስለነበር የዩልዮስ ባሕረ ሐሳብ ይባላል።

ዩልዮስ ቄሣር በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት መሠረት የዓመቱን 365 ቀናት ለስድስት ሰዓት አድርጎ ለአራቱ ወራት 30/30 ቀን ለአንዱ 28 ቀን በአራት ዓመት አንዴ 29 ቀናት፤ ለቀሩት ሰባት ወራት 31/31 ቀናት መድቦላቸው በ12 ቦታ ከፍሎታል። ለዚህም ነው በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሁሉም ወሮች 30 ቀናት ያልሆኑት። በኢትዮጵያ አቆጣጠር ግን አሥራ ሁለቱም ወራት 30 ቀናት ይሆኑና ጳጉሜ የተለየች ትሆናለች።

አውሮፓውያኑ የሚጠቀሙበት ይህን አቆጣጠር መነሻ አድርገው ነው። የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከአውሮፓውያን እንዴት እንደተለየ አሥራት ገብረማርያም «የዘመን አቆጣጠር» በሚለው መጽሐፋቸው ሲገልጹ «ዲዮናስዮስ የተባለው የሮም መነኩሴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተወለደበት ዘመን በስሌት ለመድረስ የተከተለው መንገድ የታሪክ ክስተትን ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ዘመን ለመሰወን የታሪክ ክስተትን አልተከተለችም። ቤተ ክርስቲያን የተከተለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዘመንን ነው» በማለት የልዩነቱን ምክንያት ይገልጻሉ።

የዘመን አቆጣጠር ልዩነት መነሻው የዚህ ክስተት መሆኑን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሲያረጋግጡ «ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን እንዲህ አስከትላ 5500 ብላ ስትቆጥር ዘመነ ሐዲስ ልዩ ሆኖ ከማንም ቁጥር አይገጥምም። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከምስራቆቹም ከምዕራቦቹም ሁልጊዜ በሰባት ዓመት ታጎድላለች። ምክንያቱም ባለታሪኮችን ትታ ወንጌል ተርጓሚዎችን መነሻዋ ስላደረገች ነው» ይላሉ። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ እና የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ሊኖረው ቻለ። ይሄ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ጨምሮ የዓለምን መፈጠር ምክንያት አድርጎ የተቀመረ ወጥ አቆጣጠር እንጂ ነገሥታት በተቀያየሩ ቁጥር የሚቀያየር አይደለም።

ከዘመን አቆጣጠር ስሌቷ በተጨማሪ ኢትዮጵያን ልዩ የምታደርጋት የጳጉሜን ወር ነች። ይቺ ወር አምስት ወይንም ስደስት ቀን ናት። በአራት ዓመት አንዴ ስድስት ትሆናለች። በ600 ዓመት አንዴ ደግሞ ሰባት እንደምትሆን ሊቃውንት ይናገራሉ። ይቺ አሥር ቀን እንኳን ያልሞላች «ወር» እየተባለች ትጠራለች። የቤት ኪራይ አይከፈልባትም፣ የወር ደመወዝ አይገኝባትም።

ጳጉሜን በገጠር አካባቢ «ቋግሜ» እያሉ ይጠሯታል። በጽሑፍ ደግሞ ብዙ ቦታ ላይ ጳጉሜን ቢሆንም «ጳጉሜን» እየተባለም ይጻፋል። ያም ሆነ ይህ ቃሉ አማርኛ ወይም ሌላ የአገር ውስጥ ቋንቋ ሳይሆን የግሪክ ቃል ነው። ትርጉሙም፤ ቀሪ ዕለታት፣ ቅጥያ፣ ተጨማሪ... ማለት እንደሆነ ይነገራል።

የጳጉሜን ወር ብዙ ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ክዋኔዎች ይከወኑባታል። የጳጉሜን ውሃ ከሌሎች ወራት በተለየ ቅዱስ ነው ተብሎም ይታሰባል። በዚህም ምክንያት በተለይም በገጠር አካባቢ ሰዎች በማለዳ በመነሳት ሰውነታቸውን ይታጠባሉ። ጳጉሜን ሦስት ደግሞ «ሩፋኤል» ይባላል። በዚህ ዕለት ዝናብ ከጣለ ዓመቱ የሰላምና የበረከት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

ይህን ሁሉ ጥበብ የቀመሩልን እንግዲህ ሊቃውንት አባቶቻችን ናቸው። ሃይማኖታዊም ይሁን ሳይንሳዊ፣ ባህላዊም ይሁን ዘመናዊ ይህን የመቀመር ጥበባቸው የሥልጣኔ ጀማሪዎች እንደነበርን ማሳያ ነው።

የየትኛውንም ዓለም የዘመን አቆጣጠር ብንመለከት አንድን ክስተት መነሻ አድርጎ የተቀመረ ነው። ለዚያም ብዙ የዓለም አገሮች የሚጠቀሙት አንዲት አገር በቀመረችው ቀመር ነው። ኢትዮጵያ ግን ራሷ ቀምራ በራሷ የዘመን አቆጣጠር ትጠቀማለች። «የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን» የሚባለው ለዚህ ነው።

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ተፈጥሮንም የተከተለ ነው። ተፈጥሮ ራሱ አዲስ የሚሆንበት ነው። ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ቢዘንብ የማይበቅለው አደይ አበባ መስከረምን ጠብቆ ግን ያብባል። ዓመቱን ሙሉ የማትታየው የመስቀል ወፍ መስከረምን ጠብቃ ትታያለች። ጋራ ሸንተረሩ በአበባ ይንቆጠቆጣል። በዝናብና ጉም ጨለማ የመሰለው ጊዜ መስከረም ሲገባ ፍካት ይሆነል። እንዲህ ተፈጥሮ ሁሉ አዲስ ሲሆን የሰው ልጅ መንፈስም አዲስ ይሆናል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ መስከረም መሆኑ ተፈጥሮም ያግዘዋል ለማለት ነው።

መስከረምን የተመለከቱ ሌሎች የጥበብ ሥራዎችን ሳምንት እንመለስባቸዋለን።

መልካም አዲስ ዓመት!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የአውድ ዓመት ዋዜማን በእማማ ግምጃ ቤት

ሰላማዊት ውቤ

እማማ ግምጃ ሮባ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሚደግፋቸው አቅመ ደካሞች አንዷ ናቸው። የዛሬ አራት ዓመት የለውጡ ማግስት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጠየቀው መሰረት በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ አማካይነት በደሃ ደሃ ተመልምለው አውድ ዓመትን ምክንያት በማድረግ እንዲደግፋቸው ከተሰጡት አምስት አቅመ ደካማ እናቶች አንዷ ሲሆኑ፤ የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞችም ቃላቸውን አክብረው ድጋፍ እያደረጉ ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራሮቹ እንደ ወትሮው ሁሉ ድጋፋቸውን ሊያደርጉላቸው በአዲስ ዓመት በዓል ዋዜማ እማማ ግምጃ ቤት ተገኝተዋል። የዕድሜ ጫና መነሳት ስላላስቻላቸው አልጋቸው ላይ ቁጭ እንዳሉ ነው የተቀበሏቸው። ዕድሜ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት በላያቸው ላይ ሲፈራረቅ የኖረው ድህነት እንዳደከማቸውና አቅም እንዳሳጣቸው ያስታውቃሉ። በድምጻቸው ለይተው እከሌ ነህ፤ እከሊት ነሽ ይበሏቸው እንጂ ዓይናቸው ማየት ተስኖታል። ሰውነታቸው አልታዘዝልሽ በማለቱ እንቅስቃሴ የናፈቀው እግራቸውም ድልድል ብሎ አብጧል።

እማማ ግምጃ በዚህ ባሉበት ሁኔታ የአውድ ዓመት ዋዜማ በመጎብኘታቸው ደስታ የፈነቀለውን ሳቃቸውን መሸሸግ አልቻሉም። በየወሩ የተወሰኑት የድርጅቱ አመራሮች እያዋጡ በሚሰጧቸው ፲ሺህ 800 ብር ላይ አውድ ዓመቱን ምክንያት በማድረግ ሌሎች ጥቂት ሠራተኞች አዋጥተው ያከሉበትን የበዓል መዋያ አራት ሺህ ብር የድርጅቱ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና የይዘት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ከተማ ሲሰጧቸው ደስታቸውን መቆጣጠር ተሳናቸው። እጃቸውን እንቅ አድርገው ይዘው ደጋግመው እየሳሙ የማያቋርጥና የተለመደ ምርቃታቸውን አዥጎደጎዱት።

የአቶ ፍቃዱን እጅ ሳይለቁ ዶሮና እንቁላል ጨምሮ ለበዓል የሚያስፈልገውን ገዝቶ እንዲመጣም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከወደ ጓዳ ልጃቸውን ተጣሩ። ልጃቸው መንግስቱ በፍጥነት ከጓዳ ብቅ ‹‹ብሎ ምን ልታዘዝ ›› አላቸው። ፈጣሪ በላከላቸው ገንዘብ ለአውድ ዓመት የሚያስፈልጋቸውን ገዝቶ ለመምጣት ስላበቃው በቀለጠ እልልታ እያመሰገኑት ገንዘቡን ሰጥተው ላኩት።



ፎቶ፡- ሀዲስ አብርሃ

የፕሬስ አመራሮች በአዲስ ዓመት ዋዜማ እማማ ግምጃ ቤት

ሰርቶ እሳቸውን ማስተዳደር ባለመቻሉ ባደረበት ጭንቀት የአእምሮ ህመምተኛ የነበረ ልጃቸው አሁን ላይ በተደረገለት ህክምና ከበሽታው ማገገም ቢችልም ዛሬም ቢሆን ሰርቶ ለእናቱና ለእሱ መሆን የሚችልበት ሁኔታ ላይ አይደለም። እሳቸውም ህመማቸው እየተባባሰና ከዕድሜ ጫና ጋር እየደቆሳቸው ስለመጣ ለልጃቸው እንዲቆዩለት የሚያስችል ሕክምና የሚያገኙበትን እንዲያመቻቹላቸውም በምስጋናና በምርቃት በማጀብ አሳሰቡ።

የእማማ ግምጃ ምርቃት በዚህ ብቻ አላበቃም። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራሮች ከለውጡ ጀምሮ ለተከታታይ አራት ዓመታት በአውድ ዓመትና ሰርክ በጋራም በተናጠልም ሲያደርጉላቸው የነበረውን ድጋፍ እያስታወሱ መረቁ።

እማማ ግምጃ ከዚህ ቀደም “የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያየ መልኩ ትኩረት አግኝቼ እንድታወስ በማድረጉ በ2014 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ፈርሶ የነበረው ቤቴ በተለየና ባማረ መልኩ ተገንብቶልኛል።ከሶፋ፣ ቴሌቪዥንና ምጣድ ጀምሮም አስፈላጊውን የቤት ዕቃ አሟልቶልኛል። ነገር ግን የቀድሞ ቤቴ ምንም ያህል ቢፈርስና በእንጨትና በአሮጌ ቆርቆሮ ተደጋግፎ ቆሞ የነበረ ቢሆንም እኔን የመሰሉ አቅመ ደካሞች ወለሉ ላይ ተኝተው አድረው ማልደው እንዲወጡ አከራይቼ 700 ብር አገኝና ዳቦም ሆነ እንጀራ በመግዛት ቀለቤን እሸፍን ነበር። ቤቴ ከተሰራ በኋላ ግን ይሄን ባለማድረጌ ተርቤያለሁ። አንተ ለፋሲካ እንዳደረክልኝ ሁሉ አልፎ አልፎ እየመጣህ ብትደጉመኝም አንዳንድ ኃላፊዎችም ቢደግፉኝም ዘላቂ አይደለም። የኑሮ ውድነቱን መቋቋም ባለማቻሌ ተቸግሬያለሁ” ብለው ነበር። ከዚህ መልዕክት በኋላ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌትነት ታደሰ በግላቸው ከነቤተሰቦቻቸው መጥተው ጾማቸውን ያስፈቷቸው መሆኑንና በዓሉን አብረዋቸው ማሳለፋቸውንም አብራሩ።

ሥራ አስኪያጁ አቶ ጌትነት የትንሳኤ በዓልን ከእማማ ግምጃ ጋር ባሳለፉበት ወቅት የእማማ ግምጃ ምርቃት ይድረሳችሁ በሚል የምርቃቱን አጭር አንጀት የሚበላ የቪዲዮ መልዕክት ለሠራተኛው አጋርተው ነበር።

ብዙ ሠራተኞች በግልም በጋራም ወደ እማማ ግምጃ ቤት እየሄዱ የየራሳቸውን ድጋፍ አድርገዋል። በየጊዜው ሳይቋረጥ እየተሰጣቸው ያለው ፲ሺህ 800 ብርም አመራሩ የወሰነው በዚህ መልኩ ነበር።

ምክትል ሥራ አስኪያጁ አቶ ፍቃዱ ከተማ እንደሚሉት፤ ድርጅቱ ለአቅመ ደካሞች፣ ለአረጋዊያን፣ለአካል ጉዳተኞች፣ ለተማሪዎችና በተለያየ ችግር ውስጥ ላሉ ወገኖች፣ ለመከላከያ ሠራዊት በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ እያደረገ ያለው ድጋፍ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣባቸው ካሉ ተግባራት አንዱ ሲሆን፤ ተግባሩ በተለይ እንደ እማማ ግምጃ ላሉ አረጋዊያን ስለሳቸው የሚያስብ አይዞሽ ባይ መኖሩን ተገንዝበው ተስፋ እንዲኖራቸው ያስችላል። ጤናና ዕድሜንም ሊጨምር ይችላል። ኅብረተሰቡም በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሰረታዊ ፍጆታዎች፣ በግንባታ እቃዎችና በሌሎች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት በማረጋጋትም ሆነ የመረዳዳት እሴትን በማጠናከር ረገድ አስተዋጽኦው የጎላ ነው።

በኢትዮጵያውያን መካከል ያለ ቤተሰባዊ ፍቅር፣ መተሳሰብ፣ መረዳዳት እና ትውውቅ በማሳደግ አንድነትና ማህበራዊ ሕይወት ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል። የላላውን የአገርን ሉዓላዊነት ማገርም የሚያጠብቅና ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው ብለዋል።

ጽሑፋችንን ከማሳረጋችን በፊት ስለሳቸው ትንሽ ስለ እማማ ሮባ እንንገራችሁ። ግምጃ ሮባ ዕድሜያቸውን በውል አያውቁትም። ሆኖም ፊደል ያልቆጠረው ብልህ አእምሯቸው የመጀመሪያው የጣሊያን ጦርነት የተጀመረ ዕለት ሰላሌ መወለዳቸውን ከወላጆቻቸው የሰሙበትን ደህና አድርጎ መዝግቧል።

ከትውልድ ቀያቸው ከመጡ በኋላ በአዲስ አበባ ለበርካታ አመታት ኖረዋል።በልማት ምክንያት ከነበሩበት ተነሱና አሁን ያሉበት አራት ኪሎ ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ጀርባ አካባቢ ተለዋጭ ቤት ተሰቷቸው እየኖሩ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## በአርሜኒያ እና አዘርባጃን መካከል በተቀሰቀሰ አዲስ ግጭት በርካቶች ተገደሉ

በአጎራባቾቹ አርሜኒያ እና አዘርባጃን መካከል በተከሰተ አዲስ የድንበር ግጭት በርካታ ወታደሮች መገደላቸው ተገለጸ። የአርሜኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር ኒኮላ ፓሺንያን ማክሰኞ መስከረም 03/2015 ዓ.ም. ሌሊት ላይ ባጋጠመው ግጭት 49 የአገሪቱ ሠራዊት አባላት መገደላቸውን ገልጸዋል።

እነዚህ በጠላትነት የሚተያዩት ጎረቤት አገራት ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ሁለት ጊዜ ጦርነት የገጠሙ ሲሆን፤ አነስተኛ የሆኑ ግጭቶች ግን በተደጋጋሚ ይከሰታሉ። በቅርቡ ተካሂዶ የነበረው ጦርነት በተኩስ አቁም ስምምነት እንዲጠናቀቅ ማድረጓን ሩሲያ ብትገልጽም፣ አርሜኒያ ግን ግጭቱ ለጊዜው ጋብ ብሎ ቆየ እንጂ ጦርነቱ ሙሉ በሙሉ አልቆመም ትላለች።

አርሜኒያ እና አዘርባጃን በተደጋጋሚ ለግጭት የሚዳርጋቸው ናጎረኖ-ካራባክህ በተባለው የድንበር አካባቢ በሚያነሱት የይገባኛል ጥያቄ ነው። በዚህ አወዛጋቢ አካባቢ ዓለም እውቅና የሰጠው ለአዘርባጃን ይሁን እንጂ አብዛኛው ነዋሪ ግን አርሜናዊያን ናቸው።

ሁለቱ ጎረቤት አገራት ልዩነታቸው ፖለቲካ ብቻ አይደለም። አብዛኛው የአርሜኒያ ዜጋ የክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን፣ በተቃራኒው ከአዘርባጃን ሕዝብ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ሙስሊሙ ማኅብረሰብ ነው። ሁለቱ አገራት እአአ በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ ወደለየለት ጦርነት ገብተው ነበር። እአአ 2020 ደግሞ ለስድስት ሳምንታት የዘለቀ ደም አፋሳሽ ጦርነት አካሂደው ነበር።

ሰኞ ምሽት ተቀስቅሶ ለበርካታ ወታደሮች ሞት ምክንያት ለሆነው ግጭት አንዳቸው ሌላኛውን ተጠያቂ ያደርጋሉ። አርሜኒያ አዋሳኝ ድንበር ላይ የሚገኙ ከተሞቿ በአዘርባጃን ከባድ መሳሪያ ከተደበደቡ በኋላ፣ የአጸፋ ምላሽ መስጠቷን ትገልጻለች።

አዘርባጃን በበኩሏ ወታደራዊ እርምጃ የወሰደችው ጦሯ ላይ ጥቃት ከተሰነዘረ በኋላ መሆኑን ትናገራለች።



ሞስኮ ማክሰኞ ንጋት ላይ ግጭቱ በአስቸኳይ እንዲቆም ከማደራደሯ በፊት ሌሊቱን ሙሉ በሁለቱ አገራት ወታደሮች መካከል የተኩስ ልውውጥ ሲካሄድ እንደነበረ ተገልጿል።

የአርሜኒያው ጠቅላይ ሚኒስትር ኒኮል ፓሺንያን ግን አዘርባጃን በአንድ ወይም ሁለት ግንባር ጥቃት ማድረሷን እንደቀጠለች ነው ይላሉ። ሰኞ ምሽት ተከስቷል በተባለው ግጭት በአዘርባጃን ጦር ላይ ጉዳት ስለመድረሱ ተገልጿል። የአገሪቱ ጦር እስካሁን በግጭቱ ምን ያህል ሰዎች እንደተገደሉ እና እንደቆሰሉ ያለው ነገር የለም።

የግጭቱን መቀስቀስ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አጥብቆ ኮንኗል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን፤ “ለግጭቱ ወታደራዊ መፍትሄ የለም” ብለዋል። ለአርሜኒያ ታሪካዊ ቅርበት ያላት ሩሲያ አሁን ላይ ያለው አለመግባባት መቀረፍ ያለበት “በፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ” መንገድ መሆን አለበት ብላለች። ሞስኮ ሁለቱም አገራት ራሳቸውን ከግጭት እንዲያቅቡ አሳስባለች።

ለአዘርባጃን የምትወግነው ቱርክ ደግሞ አርሜኒያ ከጠብ ጫሪነት እራሷን መግታት አለባት ብላለች። የቱርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማቭሉት ቻቩሾሉ፤ “አርሜኒያ ግጭት ከመቀስቀስ ታቅባ ትኩረቷን የሰላም ንግግር ላይ ማድረግ አለባት” ብለዋል።

ሰኞ ምሽት ያጋጠመው ግጭት ከእአአ 2020 ጦርነት በኋላ የከፋው ነው ተብሏል። ከሁለት ዓመት በፊት በነበረ ጦርነት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በሁለቱም ወገን ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን ጦርነቱ በአዘርባጃን አሸናፊነት እንደተጠናቀቀ ይታሰባል።

ሞስኮ የጦርነቱን ተሳታፊዎች ካሸማገለች በኋላ አርሜኒያ ከናጎርኖ-ካራባክሃ ግዛት ጦሯን ለማስወጣት ተገዳ ነበር። በድርድሩ ስምምነት መሠረት አርሜኒያ እና አዘርባጃን ይገባኛል በሚሉት አካባቢ ሞስኮ 2ሺህ አባላት ያሉት ሰላም አስከባሪ ጦር ያሰማራች ሲሆን፣ ይህ ጦር አሁንም በስፍራው ተሰማርቶ እንደሚገኝ ቢቢሲ ዘግቧል።

## ደቡብ አፍሪካ ስሃይማኖት ሠራተኞች የሥራ ፈቃድ መስጠት አቆመች

ደቡብ አፍሪካ በተለያዩ የሃይማኖት ሥራዎች ላይ ለሚሰማሩ የውጭ ዜጎች ስትሰጥ የቆየችውን የሥራ እና ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት ማቆሟን የአገር ውስጥ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስትሩ አሮን ሞቶሳሌዲ አወዛጋቢውን ማላዊውን ሼፐርድ ቡሺሪ እና ባለቤቱ ጉዳይን በተመለከተ ምርመራ በሚያከናውነው የፓርላማ ኮሚቴ ፊት ቀርበው እአአ በ2020 በሕገ-ወጥ መልኩ የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ክስ እያለባቸው እንዴት ከአገር ሊወጡ እንደቻሉ አብራርተዋል።


ቡሺሪ የደቡብ አፍሪካ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲያገኙ ረድታችኋል በሚል አንድ ከፍተኛ የደቡብ አፍሪካ የአገር ውስጥ ጉዳይ ባለስልጣን እና አራት የተቋሙ ሠራተኞች ከስራ ታግደዋል። ደቡብ አፍሪካ ቡሺሪ ወደ ማላዊ ማምለጡን ተከትሎም ማላዊ አሳልፋ እንድትሰጣት ጥያቄዋን በይፋ አቅርባለች።

“እኛ ባለን የሰዎች የዝውውር ቁጥጥር ስርዓታችን ውስጥ ቡሽሪ እና ባለቤታቸው ከአገር መውጣታቸውን የሚያሳይ ምንም አይነት ማስረጃ እንደማያሳይ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። ይህ ማለት ግለሰቦቹ አገሪቱን ለቀው የወጡት በሕገ-ወጥ መንገድ ነበር ማለት ነው” ሲሉ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚስትሩ ሞቶሳሌዲ ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ አክለውም በአስገድዶ መድፈር እና በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ክስ የቀረበበት ሌላኛው ናይጄሪያዊ ወንጌላዊ ቲሞቲ ኦሞትሶ እንዴት የደቡብ አፍሪካን የመኖሪያ ፍቃድ እንዳገኘ ለማወቅ ምርመራ መጀመሩን ተናግረዋል።

“እኛ እያልን ያለነው ግለሰቦቹ እንደ ጎብኚዎች ብቻ መምጣት አለባቸው ነው። ነገር ግን እንደ ጎብኚ መጥተው ሥራ መሥራት ይችላሉ። ይህ ለውጥ እነዚህ የሃይማኖት ሰራተኞች ቋሚ ነዋሪ የሚሆኑበት ምንም መንገድ የለም ማለት ነው” ሲሉ ሚኒስትሩ መናገራቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት



# የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ቅዳሜ ይጀመራል

**ቦጋለ አበበ**

የ2015 ዓ.ም ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የ1ኛ ዙር መርሃ ግብር ይፋ ከተደረገ ሰንብቷል። የፊፋና ካፍ የውድድር ሰሌዳዎችን በማየት፣ ለውድድር ዝግጁ የሆኑ ስታዲየሞችን በመገምገም እና የሊጉን ስፖንሰር አስተያየት አካቶ የተዘጋጀውን የ2015 ቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር 1ኛ ዙር(የ15 ሳምንታት) መርሃ ግብር ለፕሪሚየር ሊጉ ተሳታፊ ክለቦች ተልኳል። መስከረም 20/2015 ዓ.ም በባህር ዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም የሚጀምረው ውድድር ለአምስት ሳምንታት በባህር ዳር ቆይታ ካደረገ በኋላ በድሬዳዋ ስታዲየም ከ6ኛ እስከ 10ኛ ሳምንት እንዲሁም በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስታዲየም ከ11ኛ እስከ 15ኛ ሳምንት ሊካሄድ ቀጠሮ እንደተያዘለት ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ በየክልሉ የሚገኙ ክለቦች ባለፉት ዓመታት እንደተለመደው በየአካባቢያቸው እንደ አቋም መፈተሻ የሚጠቀሙበትን የከተማ አቀፍ ውድድር ለማካሄድ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል።

ከእነዚህ ውድድሮች መካከል ትልቅ ትኩረት የሚሰጠውና በፕሪሚየርሊጉ የሚሳተፉ በርካታ ጠንካራ ክለቦችን የሚያፎካክረው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ነው። ዘንድሮ ለ16ኛ ጊዜ የሚካሄደው የአዲስ አበባ ከተማ(ሲቲ ካፕ) ዋንጫ የፊታችን ቅዳሜ እንደሚጀመር ታውቋል። ውድድሩ ኢትዮጵያ ቡና ከኢትዮ ኤሌክትሪክ እንዲሁም ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመቻል በሚያደርጉት ጨዋታ እንደሚከፈትም ተረጋግጧል።

የውድድሩ አዘጋጅ የሆነው የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከትንናት በስቲያ ባለ ድርሻ አካላት በተገኙበት በኤልያና ሞል የውድድሩን የዕጣ ማውጣት ሥነ-ሥርዓት አከናውኗል። በዚህም ውድድሩ በሁለት ምድብ ተከፍሎ የሚካሄድ ሲሆን የመክፈቻ ተጋጣሚዎቹም ቅዳሜ በ8፡00 ሰዓት ኢትዮጵያ ቡና ከኢትዮ ኤሌክትሪክ እና በ10፡00 ሰዓት ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመቻል እንደሚሆኑ ተጠቁሟል።




ውድድሩ በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስታዲየም ሲጀመርም የተመልካቾች የመግቢያ ዋጋም ይፋ ተደርጓል። በዚህም መሠረት ሚስማር ተራ 20 ብር፣ ካታንጋ 30 ብር፣ ከማን አንሼ 50 ብር፣ ጥላፎቅ 100 ብር እና ክቡር ትሪቡን 200 ብር ሆነዋል።

ውድድሩን በምድብ አንድ ተደልድለው ኢትዮጵያ ቡና፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ እንዲሁም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘንድሮ በፕሪሚየርሊጉ የሚሳተፈው ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ያከናውናሉ። በምድብ ሁለት ደግሞ ውድድሩን በርካታ ጊዜ የማሸነፍ ታሪክ ያለውና የአምናው ቻምፒዮን ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ መቻል እንዲሁም ከዓመታት በኋላ ወደ ፕሪሚየርሊግ የተመለሰው ኢትዮጵያ መድን መደልደላቸው ታውቋል።

የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን በገቢ ለማጠናከር ታስቦና ክለቦችም ለቤትኪንግ ፕሪሚየር ሊጉ ተሳትፏቸው አቋማቸውን በመለካት በኩል እንዲረዳቸው የተዘጋጀው ይኸው ውድድር ጥሩ ፉክክር እየታየበት ባለፉት በርካታ ዓመታት ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህም በየክለቦቹ የውድድር ዕድል ያላገኙ ተስፋ ሰጪ ችሎታ ያላቸው ወጣት ተጫዋቾች ራሳቸውን የሚያሳዩበት አጋጣሚን ፈጥሯል።

የዘንድሮውን የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ሁሉንም ጨዋታዎች አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ የሚዲያ አጋር በመሆን የቀጥታ ስርጭት ሽፋን እንደሚሰጥ ተገልጿል። የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ የከተማውን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዋነኛ የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን፣ የከተማው የአንድነት መገለጫ ሆኖ እንደሚቀጥል የተናገሩት የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ደረጀ አረጋ፣ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም የሚደረጉ ጨዋታዎችን የመግቢያ ዋጋም ይፋ አድርገዋል። በዚህም መሠረት የመግቢያ ቲኬቶች ከ20 እስከ 200 ብር በአማራጭ መዘጋጀታቸውንና ለስፖርት ወዳዱ ማኅበረሰብ ሲባል ዋጋው ተመጣጣኝ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ይህን ውድድር በየዓመቱ በስፖርቱ ዘርፍ ለሚያካሂዳቸው የልማት ፕሮግራሞች ራሱን በገቢ እንዲችል እና አቅሙን ለማጎልበት፣ የተሳታፊ ክለቦችም የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ለማጠናከርና ወደ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ውድድር ከመግባታቸው በፊት የእራሳቸውን አቋም ለመለካት እንዲችሉ ያካሂደዋል። ውድድሩ በየዓመቱ የተለያዩ አዳዲስ ለውጦችን እያመጣም ተሳታፊ ክለቦች ዳጎስ ያለ ገንዘብ የሚያገኙበት መሆኑ ይታወቃል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫን ቅዱስ ጊዮርጊስ ለ6 ጊዜ በማሸነፍ ቀዳሚው ሲሆን ኢትዮጵያ ቡና ለሦስት ጊዜ፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ ለሁለት ጊዜና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንድ ጊዜ አሸናፊ ሆነው ማጠናቀቅ ችለዋል።

# አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች....... አክቸወት ወልደአረጋይ ባንቃሻ
ተጠሪ...............ተስፋዬ ወልዴ ኬራጋ
ተጠሪ ለአመልካች ልጄ ሲሆን፣ ይኸው ልጄ ሚስት ሳያገባ፣ ልጅም ሳይወልድ ከምንኖርበት ከጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ቤ/ቁ 242 ከሆነው ውስጥ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ጠፍቷል:: ስለዚህ ተጠሪ ልጄ ተስፋዬ ወልዴ ኬራጋ ያለበትን ወይም አድራሻውን እናውቃለን የሚል ካለ በ17/1/2014 ዓ.ም አአከተማ የመጀመሪያ ደራጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ምድብ ፍ/ብ/ችሎት4፡00 ሰዓት ቀርቦ እንዲያስረዳ እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጉለሌ ምድብ ችሎት**

---

የባለንብረት ስም ይስሀቅ ተካ እርዳው የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B38823 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር VNKKG96360A143160 የሞተር ቁጥር 1KR-0578315 ሞዴል KSP90L-CHMGKW የሊብሬ ቁጥር 088033 ከላይ የተቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/13/2014 አመልክተዋል። ሰሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ (15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

---

የባለንብረት ስም ዘውዱ አዱኛ ዋቄ አአ 02-01- B35980 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JTFLB71J018001313 ሞዴል HZJ79L-TJMRS የሞተር ቁጥር 1HZ-0359605 የሊብሬ ቁጥር 057907 ከላይ የተቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/13/2014 አመልክተዋል። ሰሌዳው ወድቆ፣ ተርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሌ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከሳሽ፡- ኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ እና በተከሳሽ፡- ቃልኪዳን ተክሉ መካከል ስላለው ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ09/02/2015 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ለ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

---

የባለንብረት ስም ጀማል ሲራጅ መሀመድ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-12775 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር 126192 ሞዴል viberti የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0034324 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/13/2014 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ ሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በከሳሽ፡- ሃና ሳልመን ባሳሌህ ትሬዲንግ ሆልሴል ኤንድሪቴል አፍ ፉድ እና በተከሳሽ፡- ዱካ ኢንጂነሪግ እና ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ መካከል የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 14/02/2015 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል። በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

---

አመልካች፡- አቶ ኤርሚያስ ገ/እግዚአብሔር እና በተጠሪ አቶ ልዑል ሀጎስ መካከል ስላለው ውርስ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ07/02/15 ዓ.ም በ3፡40 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

---

የባለንብረት ስም ዶ/ር ሐረገወይን በቀለ ዘውዴ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A09929 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር J11E0EE9000218544 ሞዴል EE90L-AEKDEW የሞተር ቁጥር 2E-1762904 የሊብሬ ቁጥር 131831/186557 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/13/2014 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ንፋስ የየካ ቅ/ጽ/ቤትፕር**

---

ከሳሽ/አመልካች፡- ኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ
ተከሳሽ/ተጠሪ፡- ተከሳሽ አቶ ገብረሩፋኤል ዳኛው መስፍን መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 6ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች /ተጠሪዎች ለ08/02/2015 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

---

የባለንብረት ስም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-26458 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንስ MROFR22G8D0702029 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KD-A1566 የሊብሬ ቁጥር 0211505 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 4/12/2014 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከሳሽ/አመልካች የፍ/ባለመብት አቶ ምንያህል ደረጃ ማናዬ እና በተከሳሽ/በተጠሪ በፍ/ባለዕዳ አቶ ኃይለእየሱስ ደሳለኝ መከተ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት 3ኛ ንግድ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች/ተጠሪዎች በ07/02/2015 ዓ.ም በ9፡00 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

---

ከሳሽ/አመልካች፡- ኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ
ተከሳሽ/ተጠሪ፡- ሀፍቱ ገ/ስላሴ
መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 8 ፍ/ሄ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች /ተጠሪዎች ለ14/02/2015 ዓ.ም 8፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**